እናድ
# አዲስ ዘመን
ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 222 ሚያዝያ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፎቶ፦ ሐዱሽ አብርሃ

ወይዘሮ ሰብለወርቅ ታሪኩ እና አቶ አዳነ በላይ

## የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአማራና በአፋር ባደረገው ጥናት መሰረት

- በአማራ ከ1 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ቋሚ ድጋፍ ይሻሉ
- በአፋር ከ800 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት ወድሟል
- በአማራ ከ 1ሺህ217 በላይ ዜጎች ጾታዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ባከናወነው የዳሰሳ ቁጥጥር ጥናት መሰረት በአማራ ክልል ከአንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ቋሚ ድጋፍ እንደሚሹና፤ በአፋር ክልል ከ800 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት መውደሙን አስታወቀ።

በአማራ ክልል ከ1 ሺህ 217 በላይ ዜጎች የመደፈር አሰቃቂ ጾታዊ ጥቃት እንደደረሰባቸው ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአማራና አፋር ክልሎች ባደረገው የዳሰሳ ቁጥጥር ጥናት ግኝቶች ላይ በትናንትናው ዕለት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል፡፡

በእንባ ጠባቂ ተቋም የሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞችንና አረጋውያን ዳይሬክተር ወይዘሮ ሰብለወርቅ ታሪኩ በአማራ ክልል የጦርነት ቀጠና በነበሩ ሰባት ዞኖች ላይ የዳሰሳ ቁጥጥር ጥናት መደረጉን ጠቁመው፤ በአማራ

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፦ ሐዱሽ አብርሃ

ሊቀመምህራን ቀሲስ ክሩቤል



መምህር ዳዊት



እማሆይ

## የኢየሱስ ክርስቶስን ሕማም ስናስብ የተቸገሩ ወገኖችን በመጎብኘትና ለሰላም በመጸለይ ሊሆን እንደሚገባ ተገለጸ

ገጽ 4













## አማኞች የሚጾሙለትን አምላክ ትዕዛዝ በማሰብ ደቅርታን እንዲያስቀድሙ ተጠየቀ

ገጽ 4






# የመጋቢት ወር በሰው እና በንብረት ላይ ከፍተኛ አደጋ እንደተመዘገበበት ተገለጸ

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- እሳት አደጋን ጨምሮ በከተማዋ በመጋቢት ወር ብቻ የደረሱ አደጋዎች በዘጠኝ ወር ከደረሰው በላይ በሰው እና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

በበዓል ወቅት ሊከሰቱ ከሚችሉ የእሳትና ሌሎች አደጋዎች ህብረተሰቡ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡


በእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ንጋቱ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመጋቢት ወር ብቻ 388 ሚሊዮን ብር በላይ ንብረት ወድሟል፤ ይህም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከደረሰው አደጋ በ270 ሚሊዮን ብር የሚገመት ንብረት ውድመት ብልጫ ያለው መሆኑን አመላክተዋል።

በመጋቢት ወር 2013 ተመሳሳይ ወር በደረሱ አደጋዎች የስድስት ሰው ሞት፣ ሰባት ሰው አካል ጉዳት፣ 49 ሚሊዮን 500 ሺህ ብር የንብረት ውድመት እንደነበር ያስታወሱት ኃላፊው በ2014 መጋቢት ወር ግን 15 ሰው ለሞት፣ 20 ሰው ጉዳት፣ የ388 ሚሊዮን ብር ንብረት የወደመ መሆኑን ተናግረዋል።

በመጋቢት ወር 2014 በሁሉም ክፍለ ከተማዎች አደጋ የተመዘገበ ሲሆን ጉለሌ ክፍለ ከተማ ሰባት፣ ቂርቆስ ስድስት አደጋዎች ሲከሰቱ ዝቅተኛው ደግሞ ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ሆኗል።

በመጋቢት ወር የውድመት መጠኑን ከፍተኛ ያደረገውም አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ኢንዱስትሪ መንደር ላይ በአንድ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ላይ በደረሰው ከባድ ጉዳት 350 ሚሊዮን ብር በላይ ውድመት በመድረሱ ነው። በመጋቢት ወር የተመዘገበው የሰው ሞት ከእሳት አደጋ ውጭ በሌሎች አደጋዎች ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ንጋቱ ማብራሪያ በአዲስ አበባ ባለፉት ዘጠኝ ወራት መጋቢት ወርን ሳይጨምር 377 አደጋዎች አጋጥመዋል። 251 የእሳት አደጋዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ከእሳት ውጭ በጎርፍ፣ በኮንስትራክሽን፣ ተቆፍረው ክፍት የተተው ጉድጓዶች፣ የወንዝና መሰል አደጋዎች ናቸው። በከተማዋ ከጊዜ ወደ ጊዜ የአደጋ ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን የገለጹት አቶ ንጋቱ፤ 135 አደጋዎች መንስኤያቸው የታወቀ ሲሆን 242 አደጋዎች መንስኤ እስካሁን ያልታወቁና ፖሊስ እያጣራቸው ያሉ ናቸው ብለዋል።



አቶ ንጋቱ ማሞ



በዘጠኝ ወራቱ በደረሱ አደጋዎቹም የ104 ሰዎች ሞት፣ 154 ሰዎች ከባድና ቀላል ጉዳት፣ 161 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት ውድመት የደረሰ ሲሆን፤ 55 ሰዎች ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋ እንዲሁም ሶስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር የሚገመት ንብረት ከውድመት ለማዳን ተችሏል ብለዋል።

ሕይወታቸው ካለፈው ከ104 ሰዎች መካከል 13 ሰዎች በእሳት አደጋ ምክንያት ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ በሌሎች አደጋዎች ናቸው።

በበዓል ወቅት አብዛኛው ሥራ የሚከናወነው ምሽት ላይ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሰዎች መዘናጋት ስለሚኖር ህብረተሰቡ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ አሳስበዋል።

የአብዛኞዎቹ አደጋዎች የጥንቃቄ ጉድለት እና ቸልተኝነት ናቸው ያሉት በበዓል ወቅት ከፍተኛ የእሳትና የኤሌክትሪክ ምንጮች ጥቅም ላይ ስለሚውሉ ሥራዎችን በእቅድ፣ በክፍፍልና በትኩረት በማከናወንና ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን መቀነስ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ሻማና ከሰል የመሳሰሉትን በጥንቃቄ በመጠቀም አደጋን ቀድሞ መከላከል እንደሚገባም መክረዋል።

ከአቅም በላይ አደጋ ሲያጋጥም በአዲስ አበባ በሚገኙ ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጣቢያዎች፣ 939 ነፃ የስልክ መስመር እንዲሁም 0111555300 ወደ ማዕከል በመደወል ለኮሚሽን መስሪያ ቤቱ ማሳወቅና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት በተጠንቀቅ ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል።

## የወረታ ወደብና ተርሚናል በሚሌ - ኮምቦልቻ - ወረታ መስመር የሚገቡ ኮንቴነሮችን ማስተናገድ ጀመረ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በሚሌ - ኮምቦልቻ - ወረታ መስመር የሚገቡ ኮንቴነሮችን ማስተናገድ መጀመሩን የወረታ ወደብና ተርሚናል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አስታወቀ። ፡

የወረታ ወደብና ተርሚናል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ ተስፋዬ አያሌው እንዳስታወቁት፤ የወረታ ወደብና ተርሚናል በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ አስመጭና ላኪዎች የተቀላጠፈ የደረቅ ወደብ አገልግሎት እንዲያገኙ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ይታመናል፡፡

አሸባሪው ሕወሓት በፈጠረው ጦርነት የተነሳ ወደወደቡ ይመጡ የነበሩ ኮንቴይነሮች መጠን በእጅጉ ቀንሶ እንደነበር ጠቁመው፤ አሁን ላይ ግን ዕቃ የጫኑ ኮንቴይነሮች ከበፊቱ በበለጠ መጠን መግባት መጀመራቸውን ገልጸዋል። በተጨማሪ በቅርቡ የተጠገነው የጨረቲ ወንዝ ድልድይ ለአገልግሎት ክፍት በመሆኑ ኮንቴነሮች በሚሌ - ኮምቦልቻ - ወረታ መምጣት መጀመራቸውን አስታውቀዋል።

አሁን ላይ መንገዱ ክፍት በመሆኑ አስመጭና ላኪዎች ወረታ ወደብና ተርሚናልን በመጠቀም የተለመደ የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴያቸውን በተቀላጠፈ መንገድ ማስቀጠል እንደሚችሉ ተናግረዋል።

ወደቡ ከዚህ ቀደም ይደርስ የነበረውን የጊዜና የገንዘብ ብክነት ቀንሷል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ በወጪ ደረጃ ሲታይ አንድ ትልቅ ኮንቴነር ከጅቡቲ በአዲስ አበባ ወረታ ሲገባ እስከ 200 ሺህ ብር ወጪ ሲኖረው ከጅቡቲ - ኮምቦልቻ - ወረታ ሲመጣ ግን 60 ሺህ ብር ወጪ እንዳለው አስረድተዋል።

የወደቡ ተጠቃሚዎች በበኩላቸው፤ ከጅቡቲ - ሞጆ - በአዲስ አበባ አድርገው ወደ ባህር ዳርና ሌሎች የሰሜን-ምዕራብ አካባቢዎች ይጓጓዙ የነበሩ ዕቃዎችን በአቋራጭ መንገድ ከጅቡቲ -ሚሌ -ኮምቦልቻ -ወረታ መስመር ለማስገባት ወደቡ አይነተኛ መፍትሄ እንደሆናቸው ተናግረዋል።

ብዛት ያላቸው ኮንቴነሮች ማስተናገድ መጀመሩን የገለጸው የወረታ ወደብና ተርሚናል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት፤ በ2014 ዓ.ም የበጀት ዓመት ግን በአሸባሪው ቡድን ወረራ ምክንያት መንገድ በመዘጋቱ ወደቡ 1 ሺህ 520 ኮንቴነሮችን ብቻ እንዳስተናገደ አሳውቋል።

# የመዲናዋ ነዋሪ ለአካባቢው ጸጥታው የሚያደርገውን ተሳትፎ እንዲያጠናክር ጥሪ ቀረበ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- ሰላም ወዳዱ የመዲናዋ ነዋሪ ለአካባቢው ጸጥታ መከበር የሚያደርገውን ተሳትፎ በጀመረው ልክ አጠናክሮ እንዲቀጥል የአዲስ አበባ ከተማ የሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ጥሪ አቀረበ።

በመዲናዋ አልፎ አልፎ የሚታየውን አክራሪነትም ሆነ ፅንፈኝነት ለመከላከል የሕብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝነት እንዳለው ተገልጿል።

የቢሮው ኃላፊ ዶክተር ቀነዓ ያደታ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፤ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሰላም ፈላጊ ብቻ ሳይሆን በተግባር በጉልበቱ፣ በዕውቀቱ ባለው ሀብት ሁሉ እየተሳተፈ የሚገኝ ሕዝብ ነው። ሕዝቡ ለአካባቢው ጸጥታው መከበር የሚያደርገውን ተሳትፎ በጀመረው ልክ አጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ከተማዋ የሚከሰቱ ችግሮችን የፀጥታ ኃይሉ ብቻውን ሊፈታው አይችልም ያሉት ኃላፊው፤ የሕዝቡ ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

ከህብረተሰቡ ጋር በቅንጅት የሚከናወኑ የጸጥታ ሥራዎች ውጤታማ መሆናቸው ይታወቃል። በዚህ ረገድ ሥራውም በመዲናዋ በተካሄደው የሕዝባዊ ሠራዊት ሥልጠና እንደ አንድ ትልቅ አጀንዳ ተወስዶ ውይይት እንደተደረገበት አንስተዋል።

ዶክተር ቀነዓ እንደተናገሩት፤ የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ከዚህ ቀደም በሕግ ማስከበር ዘመቻ ወቅት አካባቢውን በሕዝባዊ ሠራዊት ከፀጥታ አካላት ጋር ተደራጅቶ በመጠበቅ አብነት የሚሆን ሥራ አከናውኗል። በዚህም የአካባቢው ሰላም ሳይናጋ ቆይቷል፡፡

አሁንም ይህን በጎ ተግባሩን በማጠናከር በዘላቂነት የአካባቢውን ሰላምና ደህንነት አስጠብቆ መቀጠል ይገባዋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን በከተማዋ የሚታዩት የተደራጀ ዘረፋ፣ ድብደባና ሥርቆት የመሳሰሉ ወንጀሎች ምንጫቸው ይለያይ እንጂ ለሕዝቡ ሰላምና ደህንነት አስጊ ናቸው። ችግሮቹን ከምንጫቸው ለማድረቅ ከመሥራት ጎን ለጎን አጥፊዎችን በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በተያያዘ በአዲስ አበባ ከተማ አልፎ አልፎ የሚታየውን ብሔርን፣ ሃይማኖትንና ፖለቲካን ሽፋን ያደረገ ፅንፈኝነትና አክራሪነትን ለመከላከል የሕዝብ ተሳትፎ ወሳኝነቱ የጎላ መሆኑን ገልጸዋል።

አሁንም በከተማዋ አልፎ አልፎ የሚታዩ ብሔርን፣ ሃይማኖትንና ፖለቲካን ሽፋን ያደረጉ የፅንፈኝነትና አክራሪነት ችግሮቹን ለመከላከልም በጸጥታ ኃይሎችና በሕዝባዊ ሠራዊት በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ፅንፈኝነትና አክራሪነት በማንኛውም መመዘኛ ሀገሪቱንም ሆነ መዲናዋን አይጠቅምም ያሉት ኃላፊው፤ በተለይም ሃይማኖትንና ብሔርን እንዲሁም ፖለቲካን ሽፋን ያደረጉ ፅንፈኝነቶችና አክራሪነት በየጊዜው ብቅ የሚሉና ሕዝቡም ከጸጥታ ኃይሉ ጋር ሆኖ የሚታገላቸው መሆኑን ተናግረዋል።

በሚታዩ ፅንፈኝነትና አክራሪነት ላይ በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች በኩል ደረጃ በደረጃ እየተሠራባቸው እንደሚገኝና ከግንዛቤ ማነስ ወደዚህ አጥፊ መንገድ የሚገቡ ቡድኖችና ግለሰቦች ካሉ ቢሮው በመጀመሪያ የግንዛቤ ሥራ ላይ ትኩረት እንደሚሰጥ አስታውቀዋል።

ከዚህ አልፍ ብሎ የሚፈፀሙና ሕግን በመጣስ ተግባር የሚገለፁ ድርጊቶች ሲኖሩ ደግሞ አክራሪነትም ሆነ ፅንፈኝነት በአጠቃላይ በሕገ መንግሥቱም ሆነ በሌላ መልኩ ተቀባይነት የሌላቸውምና የሕግ ማስከበር ሥራዎች ይከናወናሉ ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ከመዲናዋ ሰላምና ጸጥታ ጋር በተያያዘ በተደረገው ሕዝባዊ ውይይት ወቅት የተነሱ ችግሮችና ከመንግሥት የተሰጡ አቅጣጫዎች እንደነበሩም አንስተዋል።

በተለያየ ደረጃ የሚገለፁ የሕግ ጥሰት አዝማሚያዎች መኖራቸውና መንግሥት የሕግ የበላይነትን እንዲያስከብር የሚጠይቁ፤ የፖሊስና ጸጥታ ኃይሎች አገልግሎት በጊዜም ሆነ በቦታ ተደራሽነት፤ ከፖሊስና የጸጥታ ኃይሎች ሥነ ምግባር ጋር የተያያዘ እና የሕዝባዊ ሠራዊት መዳከም በሕዝቡ የተነሱ ዋና ዋና ቅሬታዎች ነበሩ ብለዋል፡፡



ዶክተር ቀነዓ ያደታ

የተነሱት ጥያቄዎችን ለመፍታት የሚያስችል ዕቅድ በማዘጋጀት ለጸጥታ ኃይሎች ዕቅዱን እንዲያውቁት ከተደረገ በኋላ ወደ ሥራ መገባቱን ጠቁመዋል። አፈፃፀሙንም ከሕዝቡ ጋር በመሆን ክትትል እየተደረገበት መሆኑን አስታውቀዋል።

ከሕዝብ የቀረበው አንዱ ቅሬታ ሕዝባዊ ሠራዊት ተዳክሟል የሚል ስለነበር ችግሩን ለመፍታት ለሕዝባዊ ሠራዊቱ ሥልጠና እንደተሰጠ ዶክተር ቀነዓ ገልጸው፤ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተሳትፎን ይበልጥ በማጠናከር እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

# የማቻክል ወረዳ አርሶአደሮች የተፈጥሮ ማዳበሪያን በመጠቀም ምርታቸውን እያሳደጉ መሆኑ ተገለጸ

- የወረዳውን ተሞክሮ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ለማስፋት የንቅናቄ መድረክ ተካሂዷል

**ወርቁ ማሩ**



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

በማቻክል ወረዳ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ነው፤

አማኑኤል፡- በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን የማቻክል ወረዳ አርሶአደሮች የተፈጥሮ ማዳበሪያን በመጠቀም ምርትና ምርታማነታቸውን እያሳደጉ መሆኑ ተገለጸ። የወረዳውን ተሞክሮ ወደሁሉም የክልሉ ዞኖችና ወረዳዎች ለማስፋት የንቅናቄ መድረክ ተካሂዷል።

የማቻክል ወረዳ የግብርና ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አዲሱ ካሳ እንደገለፁት፤ በወረዳው በተቀናጀ ሁኔታ በኩታ ገጠም እርሻ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በማዘጋጀት በሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ላይ የገጠመውን የማዳበሪያ እጥረት እና የዋጋ ውድነት ችግር ለመፍታት እየተሰራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ አዲሱ ገለጻ፤ የማቻክል ወረዳ በክልሉ ከሚገኙ ከፍተኛ ምርትና ምርታማነት ካላቸው አካባቢዎች አንዱ ሲሆን በተለይ የተፈጥሮ ማዳበሪያን በመጠቀም ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበ ነው።

በዚህ መሰረት ዘንድሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው ችግር የተነሳ የማዳበሪያ እጥረትና የዋጋ ጭማሪ በማጋጠሙ በበጋና በፀደይ ወራት ብቻ ይሰራ የነበረውን የተፈጥሮ ማዳበሪያ በበጋም መስራት ተችሏል።

ከዚህ በተጨማሪ ባዮ ጋዝን በመጠቀም እና ከዚህ የሚወጣውን ፈሳሽ ዩሪያ ለመተካት ከፍተኛ ሥራ እየተሰራ ሲሆን በዚህም ከ294 ሄክታር በላይ መሬት ከሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ነፃ የማድረግ ሥራ እየተሰራ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ በበርሚል ኮምፖስት ከ325 ሄክታር በላይ መሬት ከሰው ሰራሽ ማዳሪያ ነፃ የማድረግ ሥራ እየተሰራ ነው። ከባዮ ጋዝ የሚወጣው ፈሳሽ በመጠቀም ደግሞ 500 ሄክታር መሬት ከሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ነፃ የማድረግ ሥራ እየተሰራ ነው።

በሌላም በኩል በመኸር ተሰርቶ የነበረውን ኮምፖስት በማገላበጥ ከ323 ሺህ 750 ሄክታር በላይ መሬት ማልማት ተችሏል ያሉት ኃላፊው፤ በአጠቃላይ 10 ሺህ ሄክታር መሬት ከሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ነፃ ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል።

ወረዳው 40 ወንዞች እና 300 ምንጮችን በማጎልበት 110 ሺህ ኩንታል ስንዴ፣ ለማግኘት እየሠራ መሆኑንና በ329 ሄክታር መሬት ላይ ቡና በማልማት ኤክስፖርት እያደረገ መሆኑ ተጠቁሟል።

በወረዳው በአጠቃላይ 41 ሺህ 584 ሄክታር ለም መሬት ያለ ሲሆን ይህንን ሙሉ ለሙሉ በተፈጥሮ ማዳበሪያ ለመሸፈን እየተሠራ መሆኑን ኃላፊው ጠቁመዋል።

በወረዳው በአጠቃላይ የተፈጥሮ ማዳበሪያን በመጠቀም መስራት በመቻሉ ለማዳበሪያ ሊወጣ የነበረን 50 ሚሊዮን ብር ወጪ መቀነስ የተቻለ ሲሆን የምርት መጠኑንም በዘንድሮ የምርት ዘመን በ29 ከመቶ ለመጨመር ታቅዶ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በወረዳው ኮምፖስት በመጠቀም ስኬታማ ከሆኑ አርሶአደሮች መካከል አንዱ የሆኑት የደብረ ቀለሚ ቀበሌ ነዋሪው አቶ እንየው ታደለ እንደገለጹት፤ እሳቸው የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀም በመጀመራቸው ወጪያቸውን ከመቀነሳቸውም በላይ ምርታቸው እያደገ መምጣቱን ጠቁመዋል። በተፈጥሮ ማዳበሪያ የሚመረቱ ምርቶች የምግብ ጣዕም ጭምር የተሻለ መሆኑን ጠቁመዋል።

አቶ እንየው ከዚህ ቀደም 17 ከረጢጥ ዳፕ ማዳበሪያና አምስት ከረጢት ዩሪያ ማዳበሪያ ሲጠቀሙ እንደነበር ጠቁመው፤ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በመጠቀም የሰው ሰራሽ ማዳበሪያ በግማሽ ለመቀነስ እንዳስቻላቸው ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅትም 86 ሜትሪክ ኪዩብ ኮምፖስት አዘጋጅተው ለመዝራት በዝግጅት ላይ ሲሆኑ በአጠቃላይም በሄክታር 120 ኩንታል ድንች ለማምረት እየሰሩ እንደሆነም ተናግረዋል።

ሌላው የወረዳው ነዋሪ አቶ ወንድም አበጀ፣ በበኩላቸው ከአንድ ጥማድ በላይ ድንች በኮምፖስት እያመረቱ መሆኑን ጠቁመው፤ አሁን 20 ሜትር ኩብ ኮምፖስት ማዘጋጀታቸውን ተናግረዋል።

የክልሉ የግብርና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ኃይለማርያም ከፍያለው ከጉብኘቱ በኋላ እንደተናገሩት በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ በተከሰተው ችግር የተነሳ የማዳበሪያ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ቢጨምርም መንግሥት ለአርሶ አደሩ ማዳበሪያ ማቅረቡን እንደሚቀጥል ጠቁመው፤ ያም ሆኖ ግን የተፈጥሮ ማዳበሪያን በመጠቀም በርካታ ጥቅሞችን ማግኘት እንደሚቻል ተናግረዋል።

ዶክተር ኃይለማርያም እንደገለጹት፤ የክልሉ አርሶ አደር ባለፈው ዓመት በአንድ በኩል የህግ ማስከበር ሥራው ላይ እየተሳተፈ፣ በሌላ በኩል በግብርና ሥራ ስኬታማ ሥራ ማከናወኑን ጠቁመው ፤ ዘንድሮ ደግሞ ይበልጥ ስኬታማ ለመሆን እያደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ ነው ብለዋል።

የክልሉ አርሶአደር ከጥንት ጀምሮ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ሲጠቀም እንደነበር የጠቆሙት ዶክተር ኃይለማርያም፤ አሁን ደግሞ ሥራውን ይበልጥ በማስፋት ሊጠቀምበት እንደሚገባ አሳስበዋል።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት የቴክኖሎጂ ፣የምርጥ ዘር እንዲሁም ሌሎች ድጋፎችን እያደረገ መሆኑንም ኃላፊው ተናግረዋል።

እንዲህ አይነት የተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀም በሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ሊከሰት የሚችልን የአሲዳማነት እና ሌሎች ችግሮች ሁሉ በመቅረፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው የገለጹት ኃላፊው ይህ ተሞክሮ ወደሌሎች ዞኖችና ወረዳዎች ሊሰፋ ይገባዋል ብለዋል።

በእለቱ በተካሄደው የንቅናቄ መድረክ ላይ የክልልና የዞን ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም አርሶ አደሮች የተገኙ ሲሆን ተሞክሮውን ላካፈለው የምስራቅ ጎጃም ዞን ግብርና መምሪያም የመኪና ሽልማት እንደሚሰጥ የክልሉ ግብርና ቢሮ ቃል ገብቷል።



አቶ ግርማ ፍቃዱ፤

# የቡኖ በደሌ ዞን ማህበረሰቡን በማሳተፍ በአካባቢው ሰላም ማስፈን መቻሉን አስታወቀ

**ስምስም መንግሥቱ**

በደሌ ፡- በኦሮሚያ ክልል የቡኖበደሌ ዞን ማህበረሰቡን በማሳተፍ በተከናወነ ሥራ የአካባቢውን ፀጥታው ከሚያውኩ ኃይሎች በመጠበቅ ሰላም ማስፈን መቻሉን አስታወቀ፡፡

የቡኖ በደሌ ዞን ምክትል አስተዳዳሪ አቶ ግርማ ፍቃዱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከሸኔ ጋር በተያያዘ ዞኑ በጸጥታ ሥጋት የታጠረ ቢሆንም፤ በህብረተሰብ ተሳትፎ የተለያዩ የጸጥታ ሥራዎችን በማከናወን መልካም ውጤት ማግኘት ተችሏል።

የአካባቢው ማህበረሰብ “የዞኑ፣ የወረዳውና የቀበሌው ሰላም የኔ ሰላም ነው” በሚል መንፈስ ተንቀሳቅሷል ያሉት አቶ ግርማ፤ አካባቢው ሰላም ካልሆነ ወጥቼ መግባት አልችልም የሚል ዕሳቤ በመያዝ ሰላሙን በጋራ ማስጠበቅ ችሏል ብለዋል፡፡

ወጣቶችም የማህበረሰቡ ውሳኔ አካል በመሆናቸው ከዞኑ የፀጥታ አካላት ጋር በጥምረት በመስራቱ በአካባቢው በጸጥታና መረጋጋት ረገድ መልካም ተሞክሮ መገኘቱን አስታውቀዋል።

‹‹ሰላም ከሌለ ወጣቱም ሆነ ሌላው ማህበረሰብ ሰርቶ መለወጥ አይችልም›› ያሉት አቶ ግርማ፤በተለይም ከዞኑ ነዋሪ 65 በመቶ የሆነውን ወጣት በመያዝ ሰላም እንደሚመለከተውና ነገ ሀገር ተረካቢ እንደሆነ ቀርቦ የማወያየት ሥራ በተከታታይ መደረጉን አስታውሰዋል።

የግንዛቤ ሥራው በስፋት በመከናወኑ ወጣቱም ለሰላም ትልቅ ዋጋ እንዲሰጥና አክራሪዎችን እንዲታገል ዕድል መፈጠሩን አመልክተዋል፡፡

ቡኖ በደሌ ዞን የሰላም አምባሳደር መሆኗ በሌሎችም አካባቢዎች ይታወቃል ያሉት አቶ ግርማ፤ ፀጥታን የሚያውኩ ኃይሎች ወደ ዞኑ ዘልቀው ያልገቡት አካባቢው ለእነሱ ምቹ ባለመሆኑ ሳይሆን፤በሰላምና በፀጥታ ዙሪያ የዞኑ አስተዳደርና ነዋሪው እጅና ጓንት ሆነው አካባቢያቸውን በመጠበቃቸው ነው ብለዋል።

የቡኑበደሌ ዞን ከፍተኛ የጸጥታ ስጋት ካለበት የወለጋ አካባቢ ጋር በሶስት ወረዳዎች የሚዋሰን መሆኑን የተናገሩት አቶ ግርማ፤ ወጣቶችንና ሌሎች የማህበረሰቡን አካላት ባሳተፈው ሥራ ግን ዞኑ በአንጻራዊነት የተረጋጋ ሆኗል። ህብረተሰቡን ያሳተፈ የቅንጅት ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉም ተናግረዋል።

አቶ ግርማ እንዳስታወቁት፤ አሁን ላይ በተገኘው ሰላም ወጣቱ በመንግሥት በሚቀመጥ አቅጣጫ መሰረት ተጠቃሚ እንዲሆንም እየተሰራ ነው። በ2014 ዓ.ም በዘጠኝ ወር አፈጻጸም ለ41ሺ ወጣቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል። የሥራ ዕድል ለተፈጠረላቸው ወጣቶችም ወደ 51 ሚሊዮን ብር ብድር ተመቻችቶላቸዋል።

ወጣቱ ይህን የተመቻቸለት የሥራ ዕድል በመጠቀም ኑሮውን መለወጥ የሚችለው የአካባቢውንና የሀገሩ ሰላም በዘላቂነት ሲጠበቅ እንደሆነ በአግባቡ ተረድቶ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ህብረተሰቡም በቀጣይም ሰላም የማስጠበቁ ሥራ እርሱንም በቀጥታ እንደሚመለከተው ተገንዝቦ ንቁ ተሳታፊ በመሆን የአካባቢውን ፀጥታ በትብብር ማስከበር እንደሚገባው መልዕክት አስተላልፈዋል።

# በአማራ ክልል የኤሌክትሪክ ኃይል የተቋረጠባቸውን አካባቢዎች ችግር ለመቅረፍ የሰብስቴሽን ግንባታ መጀመሩ ተገለጸ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል የኤሌክትሪክ ኃይል ለረዥም ጊዜ የተቋረጠባቸን የተወሰኑ አካባቢዎች ችግር ለመቅረፍ የሰብስቴሽን ግንባታ መጀመሩን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ገለጸ።

የኮርፖሬሽኑ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የዋግኽምራ ዞን አካባቢዎች ኤሌክትሪክ የሚያገኙበት ሰብስቴሽን በአሸባሪው ሕወሓት ተነቅሎ በመወሰዱ ምክንያት እስከአሁን የኤሌክትሪክ ኃይል እያገኙ አይደለም። የላልይበላ አካባቢዎችም ኃይል ያገኙ የነበረው ከአላማጣ ሰብስቴሽን በመሆኑ በተመሳሳይ የኃይል አቅርቦት ተቋርጦባቸዋል። ወልቃይት ጠገዴ እና ሰቲት ሁመራ አካባቢዎችም የኤሌክትሪክ ኃይል እያገኙ እንዳልሆነ አክለው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት በተዘረፈው ሰብስቴሽን ምትክ አዲስ ሰብ ስቴሽን እያስገነባ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ሞገስ፤ የተጀመረው ግንባታ የኃይል አቅርቦቱን በዘላቂነት የሚፈታ ቢሆንም የሰብስቴሽን ግንባታ በባህሪው በትንሹ የአንድ ዓመት ጊዜ የሚፈልግ በመሆኑ በተያዘው በጀት ዓመት አጠናቅቆ አገልግሎት መስጠት እንደማይችል ተናግረዋል።

የሰብስቴሽኑ ግንባታ በተያዘለት ጊዜ ሲጠናቀቅ ኤሌክትሪክ የተቋረጠባቸው በዋግኽምራ ዞን ላይ ያሉ ከተሞች እንዲሁም የላልይበላ አካባቢዎች የኤሌክትሪክ ኃይል ያገኛሉ። የወልቃይት ጠገዴ እና ሰቲት ሁመራ አካባቢዎችን ችግር ለመቅረፍ ተጨማሪ የሰብስቴሽን ግንባታ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።



አቶ ሞገስ መኮንን

በላልይበላ ከተማ ያለውን ችግር በጊዜያዊነት ለመቅረፍ ኮርፖሬሽኑ ጀነሬተር ማስቀመጡን ያመለከቱት የኮምዩኒኬሽን ዳይሬክተሩ፤ ክልሉ ነዳጅ እያቀረበ ባለመሆኑ አገልግሎት እየሰጠ እንዳልሆነ ጠቁመዋል።

የአማራ ክልል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ በበኩላቸው በአሸባሪው ሕወሓት ተይዘው የነበሩ ላልይበላ፣ ሰቆጣ፣ ወልቃት ጠገዴ እና ሰቲት ሁመራን ጨምሮ ሌሎችም አዋሳኝ አካባቢዎች በአሸባሪ ቡድኑ የመብራት መሰረተ ልማት ማውደሙን ተከትሎ አካባቢዎቹ የመብራት ችግር መፈጠሩን አስታውሰዋል።

የላልይበላ ከተማ በተለየ ሁኔታ የቱሪስት መዳረሻ በመሆኑ በጊዜያዊነት ኃይል እንዲያገኙ ጀነሬተር መቀመጡንም ተናግረዋል። ሆኖም የተቀመጠው ጀነሬተር ሙሉ ከተማውን ማንቀሳቀስ እንደማይችል የጠቀሱት የቢሮ ኃላፊው፤ ዘላቂ መፍትሄ ካልተሰጠው በጀነሬተር መጠቀሙ አዋጭነት እንደሌለው ገልጸዋል።

የነዳጅ ዋጋ በዓለም አቀፍ ገበያም እየጨመረ በመምጣቱ ማህበረሰቡ ካለው የመግዛት አቅም ጋር ተያይዞ ከባድ መሆኑን ተናግረዋል። ነዳጅ መንግሥት እያቀረበ አገልግሎት መስጠት እንደማይቻልም ገልጸዋል። አካባቢው የቱሪስት መዳረሻ በመሆኑ የአካባቢው አስተዳደር ጉዳዩን እንደ አንድ ትልቅ ሥራ በማድረግ ከከተማው ነዳጅ ማደያ ባለንብረቶች ጋር በመነጋገር ችግሩን ለመቅረፍ መሥራት እንዳለባቸውም ጠቁመዋል። የክልሉ መንግሥትም ከአካባቢው አስተዳደር ጥያቄው ቢመጣ ጉዳዩን እንደሚከታተል ጠቁመዋል።

# አማኞች የሚጾሙለትን አምላክ ትዕዛዝ በማሰብ ይቅርታን እንዲያስቀድሙ ተጠየቀ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- አማኞች የሚፆሙለትን አምላክ ትዕዛዝ በማሰብ ይቅር ሊባባሉ ይገባል ሲሉ መጋቤ ሀዲስ እሸቱ አለማየሁ ገለጹ።

መጋቤ ሀዲስ እሸቱ አለማየሁ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ ወቅቱ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታዮች በፆም የሚያሳልፉበት በመሆኑ አማኞች የሚፆሙለትን አምላክ ትዕዛዝ በማሰብ ይቅርታን ሊያስቀድሙ ይገባል።

የማንኛውም እምነት አስተምህሮ እንዲሁም በጠቅላላው ዓለምም ሆነ በውስጡ ያሉት የይቅርታ ውጤቶች ናቸው፤ ፈጣሪ የሰው ልጅን ይቅር ባይል ኖሮ መልሶ ለክብር አያበቃውም ነበር ሲሉም በደልን በይቅርታ ማለፍ እንደሚገባ ተናግረዋል።

አማኝ መሆን ማለት ያመኑትን ትዕዛዝ ተቀብሎ ማክበር ማለት ነውና የየትኛውም እምነት ተከታይ የበደለውን ይቅር በማለት የፈጣሪውን ትዕዛዝ ሊያከብር እንደሚገባውም መጋቤ ሀዲስ እሸቱ ገልጸዋል።

እንደ መጋቤ ሀዲስ እሸቱ ገለጻ፤ ይቅርታ ሁለት ጥቅሞች አሉት። የበደለን ሰው ይቅር ማለት ያለፈውን በደል በመደምሰስ ቁርሾን በማስረሳት ወደፊት ችግር እንዳይፈጠር የሚያደርግም ነው።

ይቅር ብሎ በደልን መተው ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው የገለጹት መጋቤ ሀዲስ እሸቱ፤ ይቅር ማለት ራስን መጥቀም፣ ትኩስ ቁስልን በመፈወስ ያለፈውንም



መጋቤ ሀዲስ እሸቱ አለማየሁ

በደል ይቅር በማለት ራስን ካላስፈላጊ ህመም ማዳን እንደሆነም ተናግረዋል።

ይቅርታ ሁሉን መልካም ያደርጋል ያሉት መጋቤ ሀዲስ፤ በይቅርታ ዓለም ደህው እንደ መፅዋች፣ አመንዝራው እንደ ድንግል፣ በዳይ እንደ ፃድቅ በመሆን የወደቀው ይነሳል የተበደለው ይካሳል ብለዋል።

ይቅርታ ያልገባቸው ሰዎች የቆየውን ጠባሳ እየነካኩ ትኩስ ቁስል ያደርጉታል፤ ሰላማዊውን ነገር ደግሞ ወደ ቁስልነት ይቀይሩታል፤ በዚህም ራሳቸውንም በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችንም ይበድላሉ፤ ያቆስላሉም ሲሉ መጋቤ ሀዲስ እሸቱ አለማየሁ ገልጸዋል።

ሰሞነ ህማማትን በሚመለከትም መጋቢ ሀዲስ መልእክታቸውን ያስተላልፉ ሲሆን፤ በበዓሉ ላይ የአምላካቸውን ህመሙን የሚያስቡ ክርስቲያኖች ወቅቱን ያቆሰሏቸውን ሳይሆን በቁስሉ ህይወትን የሰጠውን ክርስቶስን በማሰብ ይቅር ሊባባሉ ይገባልም ብለዋል።

መጋቤ ሀዲስ እሸቱ በእጃችን ያለው ዛሬያችንን በአግባቡ ለመኖር እንዲሁም በጉጉትና ተስፋ የምንጠብቀውን ነገ ለመኖር በይቅርታ ህይወት መመለስ እንደሚገባም መክረዋል።

እግዚአብሄር የሰው ልጆችን ይቅር ብሎ ወደ መንግሥቱ እንዳስገባ የገለጹት መጋቤ ሀዲስ እሸቱ፤ እኛም ሰዎችን ይቅር ብለን ወደ ቤታችን ልናስገባ ይገባል ሲሉም መክረዋል።

በበደልና ክፋታቸው ሰውን ጎድተው ከአዕምሯቸው ለተፈናቀሉ ጥበብና ምክር፤ ከኑሮ ለተፈናቀሉ ምግብና ልብስ በመለገስ ይቅር መባባል እንደሚያስፈልግም መጋቤ ሀዲስ እሸቱ ገልጸዋል።

መጋቤ ሀዲስ እሸቱ በቅዱስ መፅሐፍ ላይ "እግዚአብሄር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ሁሉ እርስ በእርሳችሁ ይቅር ተባባሉ" የሚል ቃል መስፈሩን በመግለፅ፤ በሰሞነ ህማማት ስቅለቱን ስናስብ ይቅርታ በማድረግ መመላለስ እንደሚገባም ገልጸዋል።

# የኢየሱስ ክርስቶስን ሕማም ስናስብ የተቸገሩ ወገኖችን በመጎብኘትና ለሰላም በመጸለይ ሊሆን እንደሚገባ ተገለጸ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በሰሙነ ሕማማት ለሰው ልጆች ደህንነት ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ ስናስብ በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖችን በመጎብኘትና ለአገር ሰላም አብዝተን በመጸለይ ሊሆን እንደሚገባ የሃይማኖት አባቶችና ምዕመን ገለጹ።

አስተያየታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሰጡት ሊቀ ማእምራን ቀሲስ ኪሩቤል ኡርጌ እንደገለጹት፤ ሰሞነ ሕማማት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ኃጢያት መከራ የተቀበለበት ነው። እኛም ሕማማትን ስናስብ በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖቻችንን በመጠየቅና ፈጣሪ ለአገራችን ሰላም ይሰጥልን ዘንድ አብዝተን በመጸይ ሊሆን እንደሚገባ አመልክተዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በደላችንን በመከራው አጥፍቶ የምህረትና የሰላም ዘመን አድሎናል ያሉት ሊቀ ማእምራን ቀሲስ ኪሩቤል፤ በአሁኑ ጊዜ ግን እኛ የሰው ልጆች ደካሞች በመሆናችን መከባበርና መደማመጥ በመጥፋቱ አገራችን አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። እንደ አማኝነታችን በዘረኝነት ክፉ ሀሳብ ከመገፋፋት ወጥተን ስለአገር ሰላም አብዝተን ልንጸልይና ወደ ፈጣሪ ልናለቅስ ይገባል ብለዋል።

በዚህ ጾም ሁሉም አማኝ በደሉንና ኃጢያቱን እያሰበ ሲጾም፣ ሲሰግድና ሲጸልይ እንደቆዬ አስታውሰው፤ ፈጣሪ በአገራችን ሰላምን እንዲያበዛ፣ የዘረኝነትና የመለያየትን ሀሳብ አስወግዶ የመተባበርና መረዳዳትን መንፈስ በምድራችን ላይ እንዲያሰፍን በትህትና ዝቅ ብሎ ለፈጣሪ ትዕዛዝ መገዛት እንደሚገባ አስረድተዋል።

መጪውን ትንሳኤ በዓል ስናከብርም በዓሉን በተለያየ ምክንያት ማክበር የማይችሉትን በማሰብ፣ መልካም ሥራና መረዳዳትን በማድረግ የበኩላችን ድርሻ ልንወጣ ይገባል ብለዋል።

መምህር ዳዊት ተስፋዬ በበኩላቸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ መከራ የተቀበለው የሰው ልጆችን ዋጋ ለመክፈል እንጂ ጥፋት ኖሮበት አይደለም። በሰሞነ ሕማማት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች የከፈለውን ዋጋና ሕማም ስናስብ በችግር ውስጥ ያሉትን ወገኖቻችንን በማስታወስ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

ጧሪ ቀባሪ የሌላቸው አረጋውያን፣ አሳዳጊ የሌላቸው ህጻናትና ሌሎችም በተለያየ ምክንያት ለችግር የተዳረጉ ዜጎችን ለማሰብ የግድ ብዙ ሀብት እንዲኖረን አይጠበቅም ያሉት መምህር ዳዊት፤ ፈጣሪ ከእኛ የሚጠብቀው ካለን ላይ ጥቂት ለሌሎች እንድናካፍል በመሆኑ ሁላችንም ሌሎችን በማገዝና አለንላችሁ በማለት በዓሉን ልናከብር እንደሚገባ ጠቁመዋል።

አገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት ብዙ ፈተናዎችን አሳልፋለች ያሉት መምህሩ፤ ኢትዮጵያውያን በየዘመናቸው የገጠማቸውን ፈተና በተባበረ ክንድ በማሸነፍ ለዛሬ አድርሰዋታል። ዛሬ ግን የፈጣሪን ህግጋት ባለማክበር ከሌሎች ይልቅ ለእኔ የሚል ራስ ወዳድነት በመንገሱ አሁን ላይ እርስ በርስ እየተገፋፋንና እየተጣላን አገሪቱን ችግር ውስጥ ከተናታል ብለዋል።

አሁን ላይ በአገራችን እየታየ ያለው ችግር የእምቢታና ለፈጣሪ ያለመታዘዝ ውጤት መሆኑን ገልጸው፤ ሁላችንም ወደፈጣሪ በንስሃና በጸጸት በመመለስና እንደቀደምት ኢትዮጵያውያን አንዳችን ለአንዳችን በማሰብ አገራችን ልንታደግ ይገባል ብለዋል።

ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ እማሆይ የሻረግ አለሙ እንደሚሉት ደግሞ፤ ጾሙን ስንጾም የትንሳኤ በዓልንም ስናከብር ያለንን ለወገኖቻችን በማካፈል ሊሆን ይገባል። ፈጣሪ ለአገራችንም ሰላም ይሰጥልን ዘንድ ሌት ከቀን ልናዝንና ልናለቅስ ይገባል ብለዋል።

ሰላም ከቤተሰብ ይጀምራል ያሉት እማሆይ የሻረግ፤ በመሆኑም ከቤተሰቦቻችን ጀምሮ ከጎረቤቶቻችን ጋር ተግባብቶ መኖር ያስፈልጋል። ሰሞነ ሕማማትንና በዓለ ትንሳኤን ስናከብር እርስ በርስ በመረዳዳት፣ በመተዛዘንና በመተጋገዝ ሊሆን እንደሚገባም ገልጸዋል።

እኛ እንደ ፈጣሪ ትእዛዝ ከሄድን ፈጣሪም ለጸሎታችን መልስ እንደሚሰጥ ገልጸው፤ አገራችን ጽኑ ሰላም እንድትሆን አዘውትረን መጸለይና በትህትና ወደ ፈጣሪ መቅረብ አለብን ብለዋል።

# የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ክልል በተለያዩ ምክንያቶች ከቀያቸው የተፈናቀሉና ቋሚ ድጋፍ የሚሹ ዜጎች በድምሩ ከአንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከተፈናቀሉት ባሻገር ሴቶችና ህጻናት ለጾታዊ ጥቃት ሰለባ ሆነዋል። በተለይ በሰሜን ጎንደር 56፣ በደቡብ ጎንደር 89፣ በሰሜን ወሎ 548፣ በዋግህምራ 111፣ በደቡብ ወሎ 342፣ በሰሜን ሸዋ 119፣ በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ስምንት በድምሩ 1ሺህ217 በላይ እናቶች፣ ልጃገረዶችና አረጋውያን የመደፈር ጾታዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ በክልሉ በሚገኙ የመንግሥት፣ የግልና የሕዝብ ተቋማትና ንብረቶች እንዲሁም ሃይማኖት ተቋማት ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የከፋ ጥፋት ደርሷል።

የትምህርት፣ የጤናና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋማት በጦርነቱ ወቅት እንደ ካምፕ፣ የሕክምና መስጫና ልዩ ልዩ መገልገያ ሆነው አገልግለዋል። በተጨማሪ ተቋማቱ ሆን ተብሎ ተቃጥለዋል፤ ተዘርፈዋል ሲሉ ተናግረዋል።

በክልሉ በጦርነት ቀጠና ውስጥ በነበሩ ሰባት ዞኖች በሁሉም የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ ከፍተኛ ውድመት መድረሱን አረጋግጠናል ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሯ ከሆነ፤ በመልሶ ማቋቋም ረገድ የፌዴራል፣ የክልል መንግሥታትና የልማት አጋር ድርጅቶች፣ በሀገር ውስጥ ያሉና በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የሃይማኖት ተቋማት ከጦርነት ማግስት ጀምሮ የዕለት ደራሽ ድጋፍ ለማኅበረሰቡ ማድረስ ችለዋል።

ከዕለት ደራሽ የምግብ ድጋፍ ጎን ለጎን ጥራትና ተቀባይነት ያለው አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ባይሆንም የደረሱ ውድመቶችን መልሶ ለማቋቋምና መደበኛ የመንግሥት አገልግሎቶች እንዲኖሩ ጥረት መደረጉን አንስተዋል።

አያይዘውም ወይዘሮ ሰብለወርቅ እንደገለጹት፤ በጦርነቱ ሳቢያ በተፈናቀሉ ዜጎች ላይ የደረሰውን የአካል ጉዳት፣ የጤና መታወክና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት ረገድ ሰፊ ድጋፍ ያስፈልጋል።

ማኅበረሰቡ በደረሰበት ችግር ለስነ-ልቦና አለመረጋጋት፣ ለድብርትና መረበሽ የተጋለጠ በመሆኑ ቀጣይነት ያለው የስነ-ልቦና አገልግሎት ማመቻቸት ይገባል። የወደሙ ንብረቶችን በፍጥነት መልሶ በመገንባት መሰረታዊ አገልግሎቶችን በፍጥነት ወደ ሥራ ማስገባት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የአስተዳደር በደል መከላከል ዳይሬክተር የሆኑት አቶ አዳነ በላይ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ጥናቱ በተካሄደበት በአፋር ክልል ሁለት ዞኖች በጦርነት ምክንያት በትምህርት፣ በጤና ተቋማትና በመንግሥት ተቋማት፣ በግለሰብ ቤቶችና በዕምነት ተቋማት ላይ የደረሰው ውድመት በብር ሲሰላ ከስምንት መቶ ሚሊዮን ብር በላይ ሆኗል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በአፋር ክልል በተለያዩ ወረዳዎች የደረሱ ጉዳቶች በመረጃ ተንተርሰው ለሚመለከታቸው አካላት ቢቀርቡም መረጃውን ተንተርሶ በፌዴራልና በክልል ደረጃ በበጀት የተደገፈ ምላሽ ያለመስጠት ችግር ታይቷል።

የመንግሥትና የልማት ድርጅት በተሟላ መልኩ አገልግሎት መስጠት አለመጀመራቸው፤ ተፈናቅለው በመጠለያ ለሚገኙ ዜጎች የመድኃኒት አቅርቦት ውስንነት መኖርና ለአረጋውያን ባሉበት ዕርዳታ ያለማቅረብ ችግሮች ከብዙ በጥቂቶቹ መሆናቸውን አብራርተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዓመት በዓላቱን በመረዳዳትና በመተሳሰብ እናሳልፍ!

የያዝነው የሚያዝያ ወር ሁለት ታላላቅ ሀይማኖታዊ በዓላት የሚከበሩበት ወቅት ነው። በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የትንሳዔ እና በእስልምና እምነት ተከታዮች በኩል ደግሞ የኢድ አልፈጥር በዓላት በተከታታይ ይከበራሉ።

እነዚህን ታላላቅ በዓላት የምናከብረው ደግሞ ከሌሎቹ በዓላት በተለየ ድምቀትና መተሳሰብ ነው። በበዓላቱ ባህር ማዶ ርቆ ያለ ቤተሰብ ወደ አገር ቤት በመምጣት፣ ለቤተሰቡና ለወዳጅ ዘመድ አዝማድ የበዓል መዋያ ጭምር በመስጠት ፍቅር የሚገለጽበት ወቅት ነው። ልጆች ወላጆቻቸውን የሚጎበኙበት፤ ወላጆች ልጆቻቸውን የሚመርቁበት፤ የመተሳሰብ፣ የመረዳዳት፣ የፍቅርና የደስታ ዕለቶች ናቸው።

በመሆኑም በእነዚህ በዓላት ሁሉም ሰው ደስ ብሎት እንዲያከብር ማድረግ ያስፈልጋል። በኢኮኖሚ የተሻለ አቅም ያለው አቅመ ደካማ ጎረቤቱን በማየት እና በመጎብኘት ፤ ካለው ላይ በማካፈል ጭምር ማክበር አለበት። በዓላት ደስታ የምናገኝባቸው ጊዜያት ናቸው። ደስታን የምናገኘው በቤታችን ለበዓሉ ድምቀት የሆኑ ዝግጅቶችን፣ ምግብና መጠጦችን በማሟላት ብቻ አይደለም። ደስታ የምናገኘው ምንም የበዓል መዋያ የሌላቸውን፣ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትን፣ ትናንት ሰጪ ዛሬ ተረጂና አቅመ ደካማ የሆኑትን ወገኖቻችንን በመርዳት እና እነሱ ሲደሰቱ በማየት ጭምር መሆን አለበት።

ሰው ሁሉ ተቸግሮ እንደማይኖረው ሁሉ ደልቶትና ሞልቶት ላይኖር ይችላል። በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ሀብታም የነበሩ ከሀብት ማማ ላይ ወርደውና ደህይተው ተመልክተናል። ስለዚህ ዛሬ ያለውና በዓልን በደስታና በፈንጠዝያ የሚያከብር ነገ የሚገጥመውን አያውቅምና ዛሬ ካለው ላይ ኢኮኖሚያቸው ደካማ የሆኑ ሰዎችን መርዳት ያስፈልጋል። ካለን ላይ ተቋድሰን በጋራ መመገብ አለብን። ይሄ ለራስም ደስታን የሚፈጥር ሲሆን በፈጣሪ ዘንድም ዋጋው ከፍ ያለ ነው።

ኢትዮጵያውያን የቆየ የመረዳዳት ባህል ያለን ሕዝቦች ነን። በደስታ፣ በሐዘንና በችግር ጊዜ የምንረዳዳበት እድር፣ እቁብና ማህበር ያለን ሕዝቦች ነን። ይሄንን ባህላችንን በበዓላት ወቅትም መድገም አለብን።

በበዓላት ወቅት ደስታን የምናገኘው በተለያየ መንገድ ነው። አንዱ ለበዓላት የሚያስፈልጉ ነገሮችን አሟልቶ ከዘመድ አዝማድና ጎረቤት ጋር በጋራ በማክበር ነው። ሁሉም ሰው ሁሉም ነገር ይሟላለታል ብሎ ማሰብ አይቻልም። ሰው በዓልንም የሚያከብረው እንደ ጎረቤቱ ሳይሆን እንደ አቅሙ ነው። በአቅሙ ማድረግ የሚችለውንና የሚገባውን አድርጎ ተደስቶ በዓልን ማሳለፍም ብልህነት መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

ሌላው ደግሞ በበዓላት ወቅት ትልቅ ደስታ የሚገኘው በመስጠት ነው። ካለው ላይ በማካፈልና በማቋደስም ነው። « መስጠት መሰጠት ነው» የሚል አንድ አባባል አለ። እውነት ነው እንደመስጠት የሚያስደስት ነገር የለም። ስጦታውን እጁን ዘርግቶ ከሚቀበለው ይልቅ የሰጠ ሰው ትልቅ ደስታን ያገኛል። ውስጡ ሀሴት ያደርጋል። ሳይበላ ይጠግባል። ምክንያቱን ደስታ ላጡ ደስታ መሆን ችሏልና ለችግራቸው ደርሷልና ነው።

የበዓል መዋያ የሌላቸው ወገኖችን ሌላው በሚያከብረው መልክ እንዲያከብሩ ማገዝና በዓሉን ተደስተው ሲያከብሩ እንደማየት የሚያስደስት ነገር አይኖርም። በመሆኑም በዓልን ለራሳችን ለማክበር ስናስብና ስንዘጋጅ በአካባቢያችን እንዲሁም በቅርብ ርቀት ያሉ ያጡ፣ የተፈናቀሉ ወገኖችን በማሰብና ካለን ላይ በማካፈል መሆን አለበት።

ሌላው ደስታን የሚፈጥረው በሀቅ ሕዝብን ማገልገል ነው። በዓልን በደስታ ለማሳለፍ ባለው ገንዘብ እንደአቅሙ ሸምቶ በዓልን ለማክበር የተዘጋጀውን ማህበረሰብ ዋጋን ከአቅሙ በላይ ባለመጫን ስናገለግለው ነው። ነጋዴው በሸቀጦች ላይ የተጋነነ ዋጋ ሳይጨምር ገዢውም ሳይሳቀቅና ይህን አልችልም ብሎ ሳይፈራ መግዛት ሲችል ነው። ስለዚህ ነጋዴዎችም ህብረተሰቡ በዓላቱን በደስታ እንዲያከብሩ የማድረግ እድሉ አላቸው።

አንድም ሸማቹን የማያስደነግጡ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ግብይት በመፍጠር ሲሆን ሌላው ደግሞ የገበያ ላይ እጥረት እንዳይፈጠር ምርት ባለመደበቅ ነው። ይሄ በሀቅ ስራን መስራት ሰዎች ተደስተው በዓላቸውን እንዲያከብሩ ምቹ ሆኖ መፍጠር፤ ለአጡ ወገኖች ከመለገስ የተናነሰ አይደለም። በራሱ ትልቅ ስጦታ እና ፈጣሪንም የሚያስደስት ስራ ነው። በተጠቃሚው ዘንድም የሚያስመርቅ ይሆናል። መመረቅ ደግሞ ለዛሬ ሳይሆን ለነገ ብድር እንደማቆየት ይቆጠራል። እናም በጎ በጎ ተግባራትን በመስራት እንመራረቅ። በጎ በጎ ስራ መስራት ስምን ከመቃብር በላይ ማስቀመጥ ጭምር ነው። በአጠቃላይ የበዓላት ቀናትን ላጡ በመስጠት ፣በመረዳዳትና በመተሳሰብ ልናከብር ይገባል!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39
ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# "በሕግ አምላክ" የሚያስብለው የገበያ ጉዳይ

**ትንሳኤ አበራ**

መቼም እንደ ዘንድሮ የዋጋ ንረት ሽቅብ በፍጥነት እየተመዘገዘገ የወጣበት ጊዜ አለ ብሎ መናገር አያስደፍርም። ጣሪያ የነካው መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች የዋጋ ንረት በየዕለቱ ጭማሪ እንጂ ቅናሽ ብሎ ነገር አሳይቶ አያውቅም። ለአንድ እቃ ወይም ሸቀጥ የተሰጠው የዋጋ ግምት ጠዋት ከተተመነለት ዋጋ ፤ በሰዓታት ልዩነት በእጥፍ ይጨምራል ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ዋጋ ይጨምራል፤ ባስ ካለ ደግሞ ወዲያውኑ ከገበያ ላይ ይጠፋል ወይም አልቋል/የለም/ ወደሚባል ደረጃ ይደርሳል። እንኳን በቀናት መካከል ያለው የዋጋ ተመን ልዩነት ይቅርና በሰዓታት መካከል የሚጨምረው ጭማሪ የትየለሌ ነው።

ይህ የኑሮ ውድነት የአብዛኛውን ህብረተሰብ ኑሮ ፈታኝ እንዲሆን አድርጎታል። የመኖር ህልውናን አደጋ ጥሎታል። የሚገርመው ደግሞ ዕቃው ወይም ሸቀጡ ከመጨመር በስተቀር ቀድሞ ወደነበርበት ዋጋ ሊመለስ ቀርቶ ባለበት እንኳን ሲገታ አለመታየቱ ነው። አንድ ሰሞን ጉድ! ጉድ! ስንልለት የቆየነው የምግብ ዘይት ዋጋ ንረት እንኳን ከተሰቀለበት ጣሪያ የሚያወርደው ሳይገኝ የበላይነቱ እንደተቆናጠጠ ይገኛል። በአንድ ጊዜ ከአንድ ሺ ብር በላይ ረግጦ ወደነበረበት የሚመልሰው አጥቶ ሽቅብ እየገሰገሰ ነው። ሌሎችም ምርቶች በተመሳሳይ ዋጋቸው ወደላይ እየተመመ ይገኛል። ህብረተሰቡ የዋጋ ንረቱን የመቋቋም አቅሙ ተፈትኖ ኑሮ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉት አይነት ሆኖበት ላለመውደቅና እጅ ላለመስጠት እየተንገዳገደ ፈታኝ ኑሮን መግፋት የግድ ሆኖበታል።

ለዋጋ ንረቱ እንደምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ የኢኮኖሚ የዋጋ ግሽበት፣ የምርት እጥረት መኖር፣ የፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ የሕገወጥ ደላሎች መበራከት፣ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት እና በአቋራጭ ለመክበር የሚፈልጉ ነጋዴዎች በአምራቾች በምርቶቻቸው ላይ ዋጋ መጨመርን የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው። በተመሳሳይም የሕግ ጥስቱና ሥርዓት አልበኝነት እየተስፋፋ መምጣቱ ነጋዴው ከውጭ የሚያስገባቸውን መሠረታዊ የምግብና ሸቀጣ ሸቀጥ ምርቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥ ምርቶች ላይ ሳይቀር የተጋነነ ጭማሪ ማድረጉ ይጠቀሳል። ያም ሆነ ይህ የዋጋ ንረቱ የህብረተሰቡን ኑሮ ከድጡ ወደ ማጡ እያደረገው፤ በእጅጉ እያከበደው ይገኛል።

መንግሥት በኩል የዋጋ ንረቱ ለማረጋጋት የተለያዩ እርምጃዎች እየወሰዱ ይገኛሉ። የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት ምርቶቻቸውን በቀጥታ ለህብረተሰብ እንዲያደርሱ በማድረግ የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት እየወሰደ ያለው እርምጃ ቀላል አይደለም። ይህም ሆኖ ግን እስካሁን ባለው ሂደት የዋጋ ንረቱን ማረጋጋት ቀርቶ ባለበት እንዲቆይ እንኳን ለማድረግ በእጅጉ ፈታኝ ሆኗል። የተቀመጠውን የመፍትሔ አቅጣጫ አጥጋቢ ምላሽ አላስገኘም።

ዞሮ ዞሮ ዋንኛው ጥያቄ ታዲያ ሊሆን የሚችለው ለምን መፍትሔ ታጣለት የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ ጥናት የሚፈልግ ቢሆንም፤ እንደኔ ግን በመንግሥት በኩል የዋጋ ግሽበቱን ለማረጋጋት እየወሰደው ያለው እርምጃ ወይም አማራጭ መፍትሔ እንዳለ ሆኖ በፍጥነት ማረጋጋት ያልቻለበት ምክንያት ውስጥ ዋንኛው የሕግ ጥሰቶች መበራከትና የሕጉ ጥብቅ አለመሆን ወይም መላለት አይነተኛ ምክንያቶች ናቸው ባይ ነኝ።

ለዋጋ ንረቱ ከላይ ተጠያቂ ያደረግናቸው አካላት እንዳሉ ሆኖ ፤ ነገሩ እዚህ ለመድረሱ እነርሱ የተጫወቱት ሚና ብቻ ነው የሚል እምነት የለኝም። ይህንን ለሕገወጥ ነጋዴዎች እና ለደላሎች ብቻ የምንተወው ጉዳይ አይደለም። በዚህ በዙሪያው በርካታ ተዋናይ የሆኑ አካላት መኖራቸው ሊታወቅ ይገባል። ይልቁን ከጀርባቸው ሆነ ደብቅ እጆቻቸውን የሚሰዱ፤ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የተሰገግሰገው የሚገኙ ሌቦች ዋንኛ ተዋናዮች መሆናቸውን በደንብ ሊሰመርበትና ሊፈተሽ የሚገባው ነገር ነው።

ለዚህም ሩቅ መሄድ ሳያስፈልገን ባሳለፍነው ሳምንት የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በሕገ-ወጥ ንግድ ተሰማርተው በተገኙ ከ33 ሺህ በላይ ነጋዴዎች ላይ እርምጃ መውሰዱን አስታውቆ ነበር። ታዲያ ቢሮ እንደዚህ አይነቶች ሕገወጥ ነጋዴዎች አደብ ለማስያዝ እርምጃ ወሰድኩ ቢልም በሌላ በኩል ከሕገ ወጦች ጋር እየተመሳጠሩ የሚሰሩ ኃላፊዎችና ሠራተኞች መኖራቸው ነገሩን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ያደርገዋል። ከሰሞኑ የተሰማው ጉዳይ ይህንን የሚያጠናክር ነው።

ለአብነትም ብንጠቅስ በቦሌ ክፍለ ከተማ የንግድ ቢሮ ኃላፊ ሕገወጥ ተብሎ የታሸገ ንግድ ቤት ለማስከፈት የመቶ ሺ ብር ጉቦ ሲቀበሉ መያዙን የሚያሳይ መረጃ መገኘቱን ሰምተናል። ይህ ደግሞ በሥልጣን ተመክቶ ያሻውን ቢያደርግ ጠያቂ እንደሌለው አመላካች ነው። ሆኖም እንደዚህ አይነቱ ተግባር እጅግ አሳፋሪ ነው። ታዲያ ለማን ይነገራል ማለት ይህንን አይደለም ትላላችሁ?። ሕግ አስፈጻሚው አካል የሕዝብ አደራ ወደ ጎን በመተው ኃላፊነቱን ተጠቅሞ የራሱ ጥቅም ለማጋበዝ ሲል ከሕግ ውጭ የሆነ አካሄድ ይከተላል። ያሻውን ያደርጋል፤ የፈለገው ይፈጽማል። ይህንን በምሳሌነት አነሳን እንጂ በሚዲያ ያልተነገሩና በተጨባጭ መረጃ ያልተገኘባቸው ሕገ ወጥ ሥራዎች መበራከታቸውን ነው ከህብረተሰቡ ጋር ካለ እውነታ መረዳት የሚቻለው።

ይህንን አይነት ተግባራት ሕግን በሚያስተገብሩ የመንግሥት አካላት ዘንድ ሕግ ጥሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ መሄዱን ማሳያ ነው። ያለምንም ውጣ ውረድና ውስበስብ ችግር በአግባቡ አገልግሎት በመስጠት የሚቻልበት የአገልግሎት አሰጣጥ አሠራር የራሱን አጀንዳ ለማስፈጸም እንዲያመቻቸው አድርጎ በማወሳሰብ ከተገልጋዩ ያልተገባ ጥቅም የሚፈልጉ ባለስልጣናትም ሆነ ባለሙያዎች እየተበራከቱ መሆን እያየን እየሰማን ነው።

ይህ ደግሞ የኑሮ ውድነቱ ማናር ብቻ ሳይሆን ወደባሰ ማጥ ውስጥ የሚከት ድርጊት ነው። ይህ አካሄድ የሚቀጥል ከሆነ መንግሥትን ሆነ ሕዝብን ዋጋ ማስከፈሉ የማይቀር ነው። ስለዚህ ባለሥልጣንም ሆነ ባለሙያ የተቀመጠበት ወንበር ሕዝብ ለማገልገል መሆኑን አውቆ ለሕግ ተገዥ መሆን ሕግን መሠረት ያደረገ አሠራር በመከተል ይገባል። ዛሬ የላላ የመሰለው ሕግ ልጓም ሲጠብቅ ተደብቆ የሚቀር ነገር አይኖርም። እራስን ከሌብነትና ብልሹ አሠራር በመቆጠብ በሕጉ መሠረት በመሥራት ለሕዝብ ወገንተኛ ለመሆን ይገባል፤ ከህሊና ፍርድ ለማምለጥ መንገድ ነው።

የሕግ ወጦችና ሥርዓት አልበኞች መስፋፋት ተጠያቂነት የጎደለው አሠራርና የሕጉን መላላት በሚገባ የሚያሳይ ነው። ሕግ ለማስከበር ደግሞ የሕግ አስከባሪው ሕግ እንዲከበር ግዴታውን የሚወጣበት ፣ ሕግ አስከባሪው የድርሻ አውቆ የሚተገበርበት ነው። የራሱ ጉዳይ ተብሎ የሚታው ነገር አይደለም እንደገናም እከክልኝ ለከክልህ በሚለው አይነት የሚሠራ ሳይሆን ለሁሉም በእኩል የሚቀመጥ ነው።

አጠቃላይ አገር የምትመራው በሕግ ነው። ለዚህ ደግሞ የሕግ አስከባሪ የሆነ አስከባሪ በእጅጉ ያስፈልጋል። ሕገ ወጥነትና ሥርዓት አልበኝነት እንዳይሰፋፋ ሕግ አስከባሪው የድርሻውን ሊወጣ ይገባል። ሕግ አክባሪውም ሕግን በማክበር መብትና ግዴታውን ማስከበር ይጠበቅበታል። የኑሮ ውድነቱ በማረጋጋት በኩል ሆነ አገር ወደ ሰከነ ሰላም ለማምጣት ዋንኛው ጉዳይ የሕግ የበላይነት ማረጋገጥ ነው። ለዚህ ደግሞ መንግሥትም ሆነ ሕዝቡ የበኩሉን የየድርሻውን መውጣት ይኖርበታል ባይ ነኝ። አበቃሁ ቸር እንሰንብት።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

# በመምከንና አለመምከን የታጀበው የይዞታ ካርታና የባለጉዳዩ ምሬት

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

### እንደ መግቢያ

ጉዳዩ፣ አቶ ሳሙኤል ጣሰው እና በቀለ ገብረሕይወት የተባሉ ሁለት ግለሰቦች በይዞታ ይገባኛል ላይ ለዓመታት የተከራከሩበትና በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ ብይኖች የተሰጠበት ነው። ዳሩ ግን አንዱ ሲፈረድለት ሌላው ፍርድ ሲጓደልበት፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ አንዱ ሲረታ ሌላው ሲረታ ጠመዝማዛ መንገዶች የበዙበትን የክርክር ሂደትን የሚያሳይ ነው።

አቶ ሳሙኤል እንደሚሉት፣ "አቶ በቀለ ገብረሕይወት የእኔን ይዞታ የራሳቸው አስመስለው ለማቅረብና በተጭበረበረ መንገድ ጥቅም ለማግኘት ፈልገዋል፤" ሲሉ ይከሳሉ።

አቶ በቀለ በበኩላቸው፤ "አቶ ሳሙኤል ከህግ አግባብ ውጭ የታገደ ካርታ በመጠቀም ብሎም የመከነ ካርታ ህጋዊ አስመስሎ በመጠቀም የማይገባውን ጥቅም የሚፈልግ ይልቁንም የእኔን መብት የሚጋፋ ግለሰብ ነው" ሲሉ ይኮንናሉ። በዚህ መልኩ እንደ መግቢያ ያነሳነውን የእሰጥ አገባ ሃሳብ ዘርዘር አድርገን እንመልከተው፡-

### አቶ በቀለ እንደሚሉት፤

አቶ በቀለ ገብረሕይወት፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ስሙ ወረዳ 25 ቀበሌ 05 በአሁኑ መጠሪያው ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 081 ባለይዞታና ነዋሪ ናቸው። አቶ በቀለ ለዝግጅት ክፍላችን ይዘውት በመጡት ቅሬታ፣ በማን አለብኝነትና ህግን ባልጠበቀ አካሄድ በህጋዊ መንገድ በሚያስተዳድሩት የይዞታ ቤታቸው ላይ ድርብ ካርታ እንደወጣባቸውና ካርታውም በፍርድ ቤትና በከተማው ከንቲባ ቢሮ ትዕዛዝ እንዲመክን መደረጉን ያስረዳሉ።

ይሁንና በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማና በክፍለ ከተማው ወረዳ 10 የሚገኙ ህግ አስፈጻሚዎች የፍርድ ቤቱንና የከንቲባ ቢሮውን ትዕዛዝ ወደ ጎን በመተውና ትዕዛዙን ሊፈፅሙ እንዳልቻሉና በዚህም ምክንያት ለእንግልት መዳረጋቸው ይገልፃሉ። የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማና ወረዳ 10 የህግ አስፈጻሚ አካላት የፈጸሙብኝን በደል «ሕዝብ አይቶ ይፍረደኝ!» ሲሉ ለአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል አቤት ብለው ነበር።

የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን አመራሮች፣ ግለሰቦችና የሰነዶችን በመመርመር ያገኘውን ውጤት ለሕዝብ መፍረድ እንዲያችል ጉዳዩን ለሕዝብ አቅርቦ ነበር። አቶ በቀለ ገብረሕይወት በኮልፌ ለምለም የህብረት ሥራ ማህበር በ1997 ዓ.ም ከ500 ሰዎች በላይ በወቅቱ በነበረው መንግስት በመደራጀት ቦታው ተከፋፍሎ ሁሉም የማህበሩ አባል በራሳቸው ፕላን መሰረት ቪላ ቤት በመስራት መኖር መጀመራቸውን ያወሳሉ።

«ከወይዘሮ ታየች አጎናፍር በ1986 ዓ.ም 340 ካሬ ሜትር ይዞታ ገዝቼ በካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/122/17448/00 በቀን 23/9/1997 ዓ.ም በስሜ የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቶኛል፤ እኔም ዲዛይን በማሰራት ቤት ሰርቼ እየኖርኩኝ ባለበት ሁኔታ የእኔ አጎራባች የነበረው አቶ ሳሙኤል ጣሰው የተባለ ግለሰብ አጣና ሲሸጥበት የነበረው ሙሉ በሙሉ በመንገድ ልማት ምክንያት ሲነሳ፣ ከእኔም ሁለት ሜትር በመንገዱ ምክንያት ተነስቷል። ይሁንና በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ባሉ ሥነ ምግባር የጎደላቸው የመሬት የይዞታ ኃላፊዎች በሙስና በመመሳጠር በይዞታ ካርታዬ ላይ ደርበው ለአቶ ሳሙኤል ካርታ ሰጥተዋል» ይላሉ።

ግለሰቡ «በግድግዳዬ ላይ በአጣና፣ ብረት፣ በብሎኬት በመስራትና እንዲሁም ሸራና ላስቲክ በመወጠር በአካባቢው የማይታወቁ ሰዎችን በማከራየት ታይዋን በሚል ስም የተለያዩ የንግድ ሥራ እየሠራ እየተጠቀመ ይገኛል» ይላሉ። ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ግንባታና ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ፅህፈት ቤት፣ ለግለሰቡ በቀን 7/8/2006 ዓ.ም በቁጥር 1230/2006 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤም የተሰጠ እድሳት ፈቃድን እንዲመክን መወሰኑን ዋቢ ያደርጋሉ።

ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ግንባታና ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ፅህፈት ቤት ኃላፊው በአቶ ገረመው ንጉሴ የተፈረመ ደብዳቤ፤ «አቶ ሳሙኤል ጣሰው የተባሉት ግለሰብ በወረዳ 10 ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 434 የሆነውን ቤት እድሳት ፈቃድ መውሰዳቸውን ይታወቃል፤ ይሁንና የወሰዱት የእድሳት ፈቃድ በአጎራባች በኩል የድንበር ክርክር ስለተነሳ የተሰጠው የእድሳት ፈቃድ ይዞታነቱ የእርሶ መሆኑ ተረጋግጦና አሁን ባለው ይዞታ መሰረት ካርታው ተስተካክሎ እስኪቀርብልን ድረስ የተሰጠው የዕድሳት ፈቃድ እንደማያገለግል እናሳውቃልን» የሚል ደብዳቤም ከመንግስት አካላት ተፅፎ ነበር።

ከዚህ በኋላም ደረጃ በደረጃ እስከ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀድሞ ከንቲባ ድሪባ ኩማ ድረስ አቤቱታ ማቅረባቸውና ከንቲባውም በአስቸኳይ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋማቸውን የሚያስታውሱት አቶ በቀለ፤ ከተቋቋመው ኮሚቴ መካከልም የወቅቱ የቅሬታ ሰሚ ኃላፊ ወይዘሮ ሃይማኖት ወልደ ገብርኤልና የመሃንዲስ ኃላፊው አቶ ጌቱ ዘውዴ የተባሉ ግለሰብ ይገኙበት እንደነበር ይጠቅሳሉ።

በወቅቱም እነዚህም ኮሚቴዎች ቦታው ድረስ በመሄድ ግራ ቀኙን በማጣራት ለከንቲባው በካርታዬ ላይ ድርብ ካርታ የተሰራ እንደሆነ ሪፖርት አቅርበዋል፤ በዚህ መሰረት በ24/4/2009 ዓ.ም በነበረው ነባር ካርታዬ መሠረት እንዲስተካከልና በይዞታዬ ላይ ያለ ማንኛውም ግንባታ በማንሳት በአምስት ቀን ውስጥ ፈፅማችሁን ሪፖርት እንድታደርጉ የሚል የፅሁፍ ትዕዛዝ ከከንቲባው ፅህፈት ቤት ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሰጠቱንም ይገልፃሉ። ይሁንና ትዕዛዙ የተሰጣቸው አካላት ከግለሰቡ ጋር ባላቸው የጥቅም ግንኙነት ጉዳዩን ለመፈፀም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል» ሲሉ ነበር ለአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ቅሬታ ያቀረቡት።


አቶ በቀለ እንደሚገልጹትም፤ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ግንባታና ቁጥጥር ፅህፈት ቤት ከአዲስ አበባ ከተማ ፀረ ሙስና እና ሥነ ምግባር ኮሚሽን ጥቆማ ተሰጥቶታል። ኮሚሽኑም በቀረበለት ጥቆማ መሰረት ቦታው ድረስ በመሄድ ጉዳዩን መርምሮ አጥርቷል። ከዚህ በኋላም ከእርሳቸው ካርታ ላይ የተደረበ ካርታ መሆኑን አረጋግጫለሁ ብሏል። የግለሰቡ ድርብ ካርታ መሆኑን በማረጋገጥ ከክፍለ ከተማው ሥራ አስፈፃሚ ጋር በመሆን የተደረበው የግለሰቡ ካርታ እንዲመክን ተደርጓል ይላሉ።

### የአቶ ሳሙኤል ምላሽ

አቶ ሳሙኤል በበኩላቸው፤ ጉዳዩ አቶ በቀለ ገብረሕይወት እንደሚሉት ሳይሆን እውነታው ሌላ ነው ይላሉ። በአሁኑ ወቅት ክርክር የተነሳበትን ቦታ እርሳቸው መጋቢት 3 ቀን 1996 ዓ.ም ከሌላ ግለሰብ በግዥ ያገኙት ንብረት ስለመሆኑ ይናገራሉ። ለዚህም ማስረጃ ይሆኑ ዘንድ ግዥ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ሁሉንም ህጋዊ መስፈርቶች ያሟላ ሲሆን ዕዳ እገዳ የሌለበት፤ የሌላ ግለሰብን ንብረት ወይንም ድንበር የማይነካ ስለመሆኑም ያስረዳሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን ይዞታው ከአቶ በቀለ አቻ የሚሆን ሲሆን በመነገድ መሰረተ ልማት እንደፈረሰባቸው ይናገራሉ። ዳሩ ግን ምትክ ሌላ ቦታ ስላልተሰጣቸው በቀረው ቦታ ላይ ግንባታ አካሂደው ሥራ መጀመራቸውን ይገልጻሉ። ታዲያ አቶ በቀለ ገብረሕይወትም የራሳቸው የሆነ ይዞታ ያላቸው ሲሆን፤ ከጉርብትና ውጭ የሚያገናኛቸው ጉዳይ እንደሌለ ያስረዳሉ።

አካባቢው የመንገድ መሰረተ ልማት እየተሰራ ሲመጣ አስፋልት መንገድ የእኔ ቤት ከግማሽ በላይ የሚሆነው ፈረሰ። ነገር ግን የቀረው ቦታ ከ75 ካሬ የማያንስ በመሆኑና በዚያው ቦታ መኖር ስለሚቻል ሕይወት ቀጠለ ይላሉ። በቀረው ቦታ ሥራ መሥራት ከመጀመራቸው ባሻገር ከቤታቸው በአንዱ አቅጣጫ ትርፍ ቦታ የነበረ ሲሆን ይህ ቦታ ደግሞ በሊዝ ከመንግስት አካላት ወደ ይዞታቸው ማካተታቸውንና ለዚህም ህጋዊ መረጃ እንዳላቸው ያስረዳሉ።

ታዲያ ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ አቶ በቀለ ገብረሕይወት ውሃ ቀጠነ በሚል ሰበብ ነጋ ጠባ ግጭት መፍጠር ጀመሩ። ነገሩ እየከረረ ሄዶ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤትም እንዳመራ ይናገራሉ። ዳሩ ግን በተለያዩ ፍርድ ቤቶችም ክርክር ቢያደርጉም በለስ አልቀናቸውም፤ ተሸነፉ። ይህን ሽንፈታውን ግን አሜን ብሎ ከመቀበል ይልቅ



በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
ADDIS KETEMA SUB CITY ADMINISTRATION
የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት
LAND DEVELOPMENT AND ADMINISTRATION OFFICE
ስልክ ቁጥር 0118-959984

ቀን 20/7/14

ቁጥር አከክከ/መልማአጽ/ቤት 14-02/14

ለአቶ ሳሙኤል ጣሰው

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በካርታ ቁጥር 10/46/1/10928በሴሪ ቁጥር 045220 የረሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ማምከንን ይመለከታል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ለ ከንቲባ ጽ/ቤት

አዲስ ተስፋ፤ አዲስ ምዕራፍ!!

በርካታ ምክንያቶችን እየደረደሩ ወረዳ፤ ክፍለ ከተማ፤ ከተማ አስተዳደር እያሉ ያንገላቱኝ ጀመር። ይህም ሆኖ በህጋዊ መንገድ ማሸነፍ ባለመቻላቸው በአስተዳደራዊ ጉዳይ እንዲታይ አሊያም ሌላ መንገድ እፈልጋለሁ እያሉ ዓመታትን በእሰጣ እገባ መጓዛቸውን ያስታውሳሉ። በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ ግን አቶ በቀለ የተዛነፈ ፍትህ እንዲሰፍን ለፍተዋል ሲሉ ይከሷቸዋል።

### ሰነዶች ምን ያሳያሉ?

አቶ በቀለ ገብረሕይወት፣ በተደጋጋሚ ከሚያነሷቸው ሐሳቦች መካከል "የመከነ ካርታ መጠቀም እና የታገደ ካርታ ጥቅም ላይ የዋለ በማስመሰል ያልተገባ ጥቅም መፈለግና የእኔን መብት መጋፋት ነው" ሲሉ ይከሳሉ። አቶ ሳሙኤል ጣሰው ግን "ይህ ወቀሳ ውሃ የማይቋጥር ይልቁንም ደግሞ በመረጃ ላይ ያልተመሰረተ ነው" በማለት፤ ከዕግድ ነፃ የሆነና ያልመከነ ካርታ እንዳላቸው ህጋዊ መረጃዎችን አሉኝ በማለት ይከራከራሉ። ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ቤት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በንግድ ፈቃድ ቁጥር 09/1/4/02156/96 የንግድ ፈቃድ ሲሆን፤ ከ10/08/ 1991 ዓ.ም ጀምሮ በየዓመቱ እያሳደሱ ሲሠሩ መቆየታውን የሚናገሩበትን መረጃ ይዘዋል።

### ከዕግድ ነፃ የሆነው ካርታ

የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት በቀን 10/11/2010 ዓ.ም በቁጥር አ/ከ/ክ/ከ/የይ/አስ/የሽ/ጊ/አገ/ፐ/ፅህፈት ቤት 168/2010 ለሰባት መንግስት ተቋማት በግልባጭ እንዳሳወቀውና ለአቶ ሳሙኤል ጣሰው በፃፈው ደብዳቤ መሰረት «ጉዳዩ፡- ታግዶ የነበረው በሴሪ ቁጥር 058762 በካርታ ቁጥር 10/46/1/10527 የተመዘገበው ካርታ እግዱ የተነሳ መሆኑን ማሳወቅን ይመለከታል በሚለው ደብዳቤ እንዲህ ያትታል።

አድራሻው አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 በቀድሞ አደረጃጀት ወረዳ 25 ቀበሌ 05 በቤት ቁጥር 434 ለተመዘገበው ይዞታ ወይንም ቤት ተሰጥቷችሁ የነበረው በሴሪ ቁጥር 058762፤ በካርታ ቁጥር 10/46/1/10527 የተመዘገበው ነባር ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳዳር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ፅህፈት ቤት በቀን 24/04/ 09 ዓ.ም በቁጥር ይመስ/1223/09 በተፃፈ ደብዳቤ አቶ በቀለ ገብረሕይወት ለክቡር ከንቲባ ያቀረቡትን አቤቱታ አስመልክቶ ጉዳዩን እንዲያጣራ የተቋቋመው ኮሚቴ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የፀደቀ ስለሆነ በውሳኔ መሰረት ተፈፃሚ እንዲደረግ ያሳወቀንን መነሻ በማድረግ በቀን 23/02/2009 ዓ.ም ለክቡር ከንቲባ ቀርቦ በጸደቀው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ለመፈፀም ይቻል ዘንድ በቀን 13/10/10 ዓ.ም በቁጥር አ/ከ/ክ/ከ/የይ/አስ/የሽ/ጊ/አገ/ፕ/ፅህፈት ቤት/19838/10 በተፃፈ ደብዳቤ ካርታው መታገዱን ያሳውቅናችሁ መሆኑ ይታወሳል።

ይሁን እንጂ ቀደም ሲል ለአቶ በቀለ ገብረሕይወት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለክቡር ከንቲባ ያቀረቡትን ቅሬታ በከንቲባ ጽህፈት ቤት በተቋቋመ ኮሚቴ በተደረገ ማጣራት በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ያቀረባችሁት ቅሬታ ተገቢነት ያለው ስለሆነ አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግ በማለት የመሬት ልማትና ማናጅመንት ቢሮ ያሳወቀውን መነሻ በማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር የሽ/ጊ/አገ/ፐ/ ፅህፈት ቤት በቀን 15/10/2010 ዓ.ም በቁጥር ይአስ/3038/10 በተፃፈ ደብዳቤ በኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት አስፈላጊው እንዲፈፀም በማለት አሳስቦናል።

በመሆኑም ለካርታው መታገድ ምክንያት የነበረው ቀደም ሲል ለክቡር ከንቲባ በቀን 23/03/2009 ዓ.ም ተዘጋጅቶ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ድጋሚ በተዋቀረው ኮሚቴ በቀን 14/10/ 2009 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ለክቡር ከንቲባው በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የተሻረ ስለሆነ በቀን 13/10/2010 ዓ.ም በቁጥር አ/ከ/ክ/ከ/የይ/አስ/የሽ/ጊ/አገ/ፐ/ፅህፈት ቤት/19838/10 በተፃፈ ደብዳቤ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

ታግዶ የነበረው በሴሪ ቁጥር 058762፤ በካርታ ቁጥር 10/46/1/10527 የተመዘገበው ካርታ እግዱ የተነሳ መሆኑን እናሳውቃለን። የሚመለከታቸው ክፍሎችም እግዱ የተነሳ መሆኑን አውቀው አስፈላጊውን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በግልባጭ እንዲያውቁት ተድርጓል ሲል አቶ ሳሙኤልን ህጋዊነት ያረጋግጣል።

## ያልመከነው ካርታ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ፅህፈት ቤት በቀን 10/11/2010 ዓ.ም በቁጥር አ/ከ/ክ/ከ/የይ/አስ/የሽ/ጊ/አገ/ፐ/ፅህፈት 167/2010 ለሰባት መንግስት ተቋማት በግልባጭ እንዳሳወቀውና ለአቶ ሳሙኤል ጣሰው በፃፈው ድብዳቤ መሰረት «መክኖ የነበረው በሴሪ ቁጥር 045220 በካርታ 10/46/1/10528 የተመዘገበው የሊዝ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወደ ነበረበት የተመለሰ መሆኑን ማሳወቅን ይመለከታል» በሚለው ደብዳቤ እንዲህ ያብራራል፡-

አድራሻው አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 በቀድሞው አደረጃጀት ወረዳ 25 ቀበሌ 05 በቤት ቁጥር 434 የተመዘገበው ይዞታ/ቤት በሴሪ ቁጥር 045220 በካርታ ቁጥር 10/46/1/10528 የተመዘገበው የሊዝ ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ በቀን 06/11/08ዓ.ም በቁጥር አ//ከ/81/ከ/የይ/አስ/የሽ/ጊዜ/አገ/ፐ/ጽ/ቤት/10412/08 በተፃፈ ደብዳቤ የመከነ ወይንም የተሰረዘ መሆኑ ይታወቃል።

ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት በቀን 27/10/2010 ዓ.ም በቁጥር ይአስ/3173/10 እንዲሁም በቀን 04/11/2010 ዓ.ም በቁጥር ይአስ/3262/10 በተፃፉ ደብዳቤዎች የፍርድ ቤት ዕግድ የሌለው መሆኑ ታይቶ ካርታቸው ወደነበረበት እንዲመለስ በማለት ያሳወቀንን መነሻ በማድረግ ባደረግነው ማጣራት ይህ ደብዳቤ ወጭ እስኪደረግ ድረስ በማህደሩ ውስጥ የተያያዙ የፍርድ ቤት ዕግድ ሰነድ ያለመኖሩን አረጋግጠናል።


ስለሆነም አድራሻው አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 በቀድሞ አደረጃጀት ወረዳ 25 ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 434 ለተመዘገበው ቤት ወይንም ይዞታ በሴሪ ቁጥር 045220 በካርታ 10/46/1/10528 የተመዘገበው የሊዝ ይዞታ ካርታ በቀን 6/11/08 ዓ.ም በቁጥር አ/ከ/ክ/የይ/አስ/የሽ/ጊዜ/አገ/ፐ/ጽ/ቤት/10412/08 በተፃፈ ደብዳቤ ተጥሎ የነበረው የይምከን ውሳኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፐ/ጽ/ቤት ከላይ ቀንና ቁጥሩ በተጠቀሱት ደብዳቤዎች የመከነው ካርታቸው ወደ ነበረበት እንዲመለስ በማለት በሰጠው ውሳኔ በይዞታ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 12/2004 አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 16.8 ድንጋጌ መሰረት የካርታ መምከኑ ቀርቶ ወደ ነበረበት የተመለሰ መሆኑን እናሳውቃለን። የሚመለከታቸው ክፍሎችም የካርታው መምከን ቀሪ የተደረገ ወይም ወደ አገልግሎት የተመለሰ መሆኑን በግልባጭ እንዲያውቀው ተደርጓል።

## የመንግስት አካላት ምላሽ

የዝግጅት ክፍላችን ጉዳዩ በዋናነት ወደሚመለከተው የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በማምራት ለማጣራት የሞከረ ሲሆን፤ በተደጋጋሚ ለሚጠይቃቸው መረጃዎች ለመተባበር ፈቃደኛ አልነበሩም። ይልቁንም የአቶ በቀለ እና የአቶ ሳሙኤል ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት ያመራ ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ላይ ለመገናኛ ብዙሃን መረጃ መስጠት የፍርድ ቤቶችን በነፃነት የመወሰን መብት ላይ ጫና ማሳደር ነው የሚል ነበር። ከዚህም በዘለለ የግለሰቦቹ ክርክር ከይዞታ ይገባኛል ይልቅ ከግንባታ ፈቃድ ጋር የተያያዘ በመሆኑ እልባት ሊሰጠው እንደሚችልም ጠቁመው ነበር። ይህ ሆኖ ሳለ ግን የአቶ ሳሙኤል ንብረት እንዲወረስና እንዲፈርስ ተደርጓል። ጉዳዩ በህግ ሂደት ላይ ከሆነ ሰሞኑን የአቶ ሳሙኤል ቤት ንብረት መፍረሱና መወረሱ ስለምን አስፈላጊ ሆነ ለሚለው ምላሽ ለማግኘት በተደጋጋሚ ስልክ ብንደውልም መረጃ ማግኘት አልተቻለም።

## በአንድ ራስ ሁለት ምላስ

የአቶ ሳሙኤል ጣሰው ይዞታ ህጋዊ ስለመሆኑ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በተደጋጋሚ ማረጋገጫ ሰጥተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ይዞታው ቀደም ሲል ከሌላ ግለሰብ በግዥ ያገኙት ነው። በአካባቢው የመንገድ መሠረተ ልማት ሲሠራ ቤታቸው ከእኩሌታው በላይ ያፈረሰባቸው ቢሆንም ይልቁንም


Addis Ketema Sub City Administration
Tenure Administration Transition
Period Service Project Office

Date 10/11/2010
Our Ref No ... 168 ... 2010


ለአቶ ሳሙኤል ጣሰው ገ/ሚካኤል
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ታግዶ የነበረው በሴሪ ቁጥር 058762፤ በካርታ ቁጥር 10/46/1/10527 የተመዘገበው ካርታ እግዱ የተነሳ መሆኑን ማሳወቅን ይመለከታል፤

[illegible]

TESFAYE BOGALE WEDAJO

0118-67-85-17


Addis Ketema Sub City Administration
Tenure Administration Transition
Period Service Project Office

Date 10/11/2010 ዓ.ም
Our Ref No ... 167 ... 2010

ለአቶ ሳሙኤል ጣሰው ገ/ሚካኤል
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- መክኖ የነበረው በሴሪ ቁጥር ቁጥር 045220 በካርታ 10/46/1/10528 የተመዘገበው የሊዝ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወደ ነበረበት የተመለሰ መሆኑን ማሳወቅን ይመለከታል፡፡

[illegible]

TESFAYE BOGALE WEDAJO

0118-67-85-17

ደግሞ ለዚህ ቦታ ምትክ ያልተሰጣቸው መሆኑ እየታወቀ የክፍለ ከተማው አስተዳደር በቀን 20/7/14 ዓ.ም የመከነ ካርታ ስለመሆኑ ደብዳቤ ፅፏል። ክፍለ ከተማው ይህን ደብዳቤ ይፃፍ እንጂ ቀደም ሲል ይህ የአቶ ሳሙኤል ይዞታ ህጋዊ ስለመሆኑ ለበርካታ ጊዜያት በሰጠው መረጃ እና ደብዳቤ አሳውቋል። ይህም ሁሉ ሆኖ ሳለ በቀን 20/7/14 ዓ.ም የተፃፈው ደብዳቤ ይዞታው ህጋዊ አይደለም ይፍረስ የሚል አልተካተተበትም። ግን ከመቅፅበት የአቶ ሳሙኤል ንብረት ወደፍርስራሽ ተቀይሯል።

ክፍለ ከተማው በቀን 20/7/14 ዓ.ም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ፅህፈት ቤት፤ «ጉዳዩ፡- በካርታ ቁጥር 10/46/1/10/928 በሴሪ ቁጥር 045220 የተሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ማምከንን ይመለከታል» በሚል ደብዳቤ በቀን 20/7/2014 ዓ.ም በቁጥር አከክከ/መልማት ፅ/ቤት 14-02-14፤ ለአቶ ሳሙኤል ጣሰው በጻፈው ደብዳቤ እና ለ10 ተቋማት በላከው ግልባጭ እንዲህ ሲል ያትታል፡-

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የካርታ ቁጥር 10/46/18/10528 የሴሪ ቁጥር 045220 የሆነ ካርታ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የቤት ቁጥር 434 ለሆነ ቤት ተሰጥቶት የነበረና ከአሁን በፊት 6/11/08 ዓ.ም በቁጥር አ/ከ/ክ/ከ/የይዞ/አስ/የሽ/ጊዜ/አገ/ፐ/ጽ/ቤት/0412/2008 በሆነ የመከነ መሆኑ ተገልፆልዎት ባቀረቡት አቤቱታ በድጋሚ በቁጥር 167/2011 በቀን 10/11/2010 ዓ.ም ወደነበረበት ተመልሶ ነበር።

ነገር ግን በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመለያ ቁጥር 245802 በቀን 29/08/2010 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የካርታው መምከን አግባብ ነው የሚል ውሣኔ በመስጠቱ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ በቁጥር አአ/መልአቢ/212/3499/2014 በቀን 09/7/ 2014 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ካርታው በመከነው አግባብ እንዲፀና መክኖ የነበረው ካርታ ወደነበረበት ተመልሶ ከሆነም ደግሞ እንዲመክን እንዲደረግ ያሣወቅን በመሆኑ ከቢሮው በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት በካርታ ቁጥር 10/46/1/10928 በሴሪ ቁጥር 045220 በቤት ቁጥር 434 ለሆነ ቤት ተሰጥዎት የነበረ ካርታ በይዞታ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 12/2004 መሠረት የመከነ መሆኑን እያሣወቅን ግልባጭ የተደረገላችሁ መስሪያ ቤቶች ጥንቃቄ እንድታደርጉ እናሣውቃለን ሲል በተደጋጋሚ ጊዜ የአቶ ሳሙኤል ካርታ አለመመከኑን እና አለመታገዱን በገለፀበት አንደበት መልሶ ለአቶ ሳሙኤል የተሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መመከኑን ይገልፃል።

## አቶ ሳሙኤል ይጠይቃሉ!

እነዚህ ሁሉ ህጋዊ ሂደቶች ታልፈው እንዲሁም ሁኔታዎች ሁሉ መረጃዎችን መሰረት አድርገው እየሄዱ እያሉ ስለምን ዱብ ዕዳ ወረደ? ሲሉ ይጠይቃሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፤ በህግ አግባብ እንደሚታየውና ሁኔታዎችን መረዳት እንደሚቻለው ሰው ህጋዊ ይዞታው ስለምን እንዲቀማ ይወሰናል ይላሉ። ንብረት ማውደም ቤት ማፍረስ እና መቆራረጥስ ከምን የመነጨ ነው ሲሉም ይጠይቃሉ። እልባት ባላገኘ ጉዳይ ላይ የመንግስት አካላትም ያለ አንዳች ማስጠንቀቂያ የግለሰብን ንብረት ማፈረስና ማውደም ዓይን ያወጣ የመብት ጥሰት መፈጸም በየትኛው ህግ ይዳኝ ይሆን ይላሉ። ለመሆኑ መፍረስ ቢኖርበት እንኳን ግለሰቦች ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው አይገባምን፤ ንብረትስ በሥርዓት እንዲነሳ አይደረግም? በመንግስት አካላትና በተዋረድ በሚመለከታቸው ህጋዊ አካላት ምንም ሳይነገርና በደብዳቤ ሳያሳውቁ የግለሰብን ንብረት ከጥቅም ውጭ እንዴት ሊደረግ ይችላል ሲሉ ግራ በመጋባት ስሜት ይጠይቃሉ።

ከምንም በላይ ይዞታው ያልመከነ ካርታ እና በዚህ አግባብ እገዳ የሌለበት መሆኑን ማስረጃ እያለ መልሶ ራሱ ክፍለ ከተማው የሚጣረስ ተግባር ውስጥ ለምን እንደገባ ለማወቅ መቸገራቸውን ይናገራሉ። ይህም ሆኖ ሳለ አፍራሽ ግብረ ኃይሎች በድንገት መጥተው ማፍረሳቸው ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የሆነ የመብት ጥሰት መፈፀማቸውንና ኃይል መጠቀማቸው በእጅጉ እንዳሳዘናቸው ይናገራሉ። ታዲያ ይህን መሰል ዓይን ያወጣ ድፍረትና የመብት ጥሰት ወደየት አቤት ማለት ይቻላል ሲሉ ፍትህ መጠማታቸውን ይናገራሉ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ቅርስ አናርክስ

## "ቅርስ እንደ ኩል" - የማዋዣ ወግ፤

ቅርስና ኩልን ምን ያገናቸኛዋል? ምንም አያገናኛቸውም። "እንደ" ተብለው በተነጻጻሪ አያያዥ መጣመራቸው ለርዕሰ ጉዳያችን ማዋዣነት ይበጁ ይሆን ብለን በማሰብ እንጂ አንዱ ከአንዱ ጋር የባህርይም ሆነ የተፈጥሮ ዝምድና የላቸውም። ኩል የወይዛዝርት መኳኳያና መዋቢያ ነው። ለዐይን ጥራትና ቁርቋሬም እንደ መፍትሔ ተቆጥሮ ከመድኃኒት ዝርያ ጋር የሚያዛምዱ ግለሰቦችም እንዳሉ ይታወቃል።

ኩል የተፈጠረበት ዋናው ዓላማ ለመዋቢያነት አገልግሎት ስለሆነ ተዘውትሮ የሚኀዳኘው ለቅንድብና ለሽፋሽፍት መሽቀርቀሪያነት እንጂ፤ በተቀጥያ ተግባሩ እጅግም ይወደስ አይባልም። እንዲያም ሆኖ ግን በአጠቃቀም ወቅት ጥንቃቄና መጠኑ በዝቶ ዐይን ላይ ሲሞጀር ወይዛዝርት የሚኳሉበትና "እረ ኩሉን ማን ኳለሽ" እየተባለ የሚደነቁበት ኩል መዋቢያነቱ ቀርቶ ዕይታን እየጋረደ ለእንቅፋት ይዳርጋል። ይህንን እውነታ የተረዱት እናቶች ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው ሲመክሩ፤ "ሲያጌጡ ይመላለጡ" እንዳይሆንባቸው ለማስጠንቀቅ "ባለ ኩል ያሰናክል" የሚለውን ብሂል እንደሚጠቀሙ ሥነ ቃላችን ይመሰክርልናል።

ከወይዛዝርት የመዋቢያ ኩል ጋር በስሱም ቢሆን ለማመሳሰል የሞከርነው አገራዊ ቅርስ ልክ እንደ ኩል ሁሉ የታሪክ ውበት ወይንም መቆዘሚያ ሆኖ ለትውልዶች በቅብብሎሽ የሚተላለፍ ምስክር እንጂ ራሱ ታሪክ አይደለም። ለቁንጅና ሲባል የሚመረጠው ኩል እየተመጠነና በጥንቃቄ ግልጋሎት ላይ ካልዋለ በስተቀር ዐይንን እያጥበረበረና እየቆረቆረ ለእንቅፋት እንደሚዳርግ ሁሉ፤ ለታሪካችን ምስክር ሆነው የኖሩና እንደ አንድ የአገር ጌጥ በክብር መታየት የሚገባቸው ቅርሶቻችንም እንዲሁ ወካይ እንጂ የታሪኩ ዋነኛው አካል ያለመሆናቸው እየተዘነጋ አልፎ አልፎ በእንቅፋትነት ሲነወሩ ይስተዋላል።

በተንሸዋረሩ የታሪክ አተያየቶችና አተረጓጎሞች ምክንያትም የጋራ ያልናቸው ታሪካዊ ቅርሶች ከውበታቸውና ከታሪካዊ ወካይ ፋይዳቸው ይልቅ የእርስ በእርስ መሰነካከያና እንቅፋት በመሆን በአብሮነታችን ድምቀት ላይ ጥላ እያጠሉ ብርሃናማውን የሕዝቦች ትስስርና ተጋምዶ እየጋረዱ "ባህል" ወደ መሆን ደረጃ ላይ የተደረሰ ይመስላል። የታሪኮቻችን መገለጫዎችና ውበት አድርገን ተቀብለናቸው የኖርነውና በኩል የመሰልናቸው አንዳንድ ቅርሶቻችን ከመዋቢያነት ይልቅ ለምን ጥላሸት እየሆኑ ስንጎሻሸምባቸውና ስንደነቃቀፍባቸው ውለን እንደምናድርም ልብ ተቀልብ ሆነን ልንመካከርበት ይገባል።

ቅርስ ማርከስ ታሪክን ማስኮረፍ፤

በአገራዊ ቅርስነት የምንፈርጃቸው የሕዝባችን የታሪክ ምስክሮች፣ የባህሎቻችን ውበቶችና የእምነቶቻችን ትሩፋቶች ዓይነታቸው፣ መልካቸውም ሆነ ቁጥራቸው በዋዛ ተዝርዝሮ የሚገለጽ አይደለም። የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ፣ ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ወዘተ. እያልን በፈርጅ በፈርጃቸው እየመደብን እንተንትናቸው ብንል በተከታታይ የመጻሕፍት ቅጾችም ቢሆን ሰንዶ ለማጠናቀቅ ተግዳሮቱ ቀላል እንደማይሆን መገመት አይከብድም።

በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ጥንታዊና በታሪካቸው የከበሩ አገራት ዋነኛ መታወቂያቸውና መከበሪያቸው የተትረፈረፈው የቅርስ ሀብታቸው እንደሆነ በሚገባ ይታወቃል። የአገራት የቅርስ ሀብቶች በአግባቡ ተሰንደውና ተሰድረው ከብረው እያስከበሩ እንዳይኖሩ በተለያዩ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች የተነሳ በየዘመናቱ ለአደጋ መጋለጣቸው አልቀረም። "አዋጁን በአዋጁ" እንዳይባል እንጂ በቅርሶቻችን ላይ የሚደረሱትን ውድመቶችና ዘረፋዎች፣ ዳተኝነቶችና ንዝህላልነቶች በተመለከተ ብዙ ጊዜያት ብዙ ስለተባለ በዚህ ቦታ ደግመን ነጋሪት መጎሰሙ እጅግም አስፈላጊ አልመሰለንም።

ያለመታደል ሆኖ በበረሃና በባህር፣ ኬላ አሳብረውና ወንዝ አቋርጠው ወይንም ቪዛ እያስመቱና ሕጋዊ ሰነድ እያውለበለቡ ለስደት የሚዳረጉት ዜጎቻችን ብቻ ሳይሆኑ አገራዊ ቅርሶቻችን ጭምር ናቸው። በአንዱ ዐይናችን ለዜጎቻችን፣ በሁለተኛው ዐይናችን ለቅርሶቻችን እምባ እንዳፈሰስንና በቁጭት እንደተንገበገብን እነሆ ዘመን በዘመን ላይ፤ ሥርዓትም በሥርዓት ላይ ተነባብሮ ለዛሬ ጀምበር በቅተናል።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ እንኳንም በኩብለላ እየሸሹን ላሉት ወይንም ለኮበለሉብን የሩቅ አገር ነዋሪ "ስደተኛና ምርኮኛ ቅርሶቻችን" ቀርቶ የታሪካቸው እትብት በተቀበረበት በራሳቸው ሕዝብና አገር ውስጥ የሚኖሩት ታሪክና ውበት አጣምረው የያዙት ቅርሶቻችንም ሳይቀሩ የተለያዩ የጥፋት አደጋዎች እየተጋረጠባቸው መሆኑን ተቆርቋሪ ዜጎች በነጋ በጠባ ኡኡታቸውን እያሰሙ ስለመሆናቸው አልሰማንም ማለት አንችልም። "እዚያ ሰፈር ታሪካዊ ሕንጻዎች እየፈረሱ ለባለ ሃብቶች ብሎኬት መደርደሪያነት ሊሰጡ መወሰኑን ሰምተናል" የሚሉ ኡኡታዎች ይደመጣሉ።

ወዲያ ማዶ ደግሞ "ለሥዕል ጥበብ ማሳያነት ግልጋሎት ሲሰጥ የኖረ ታሪካዊ ሕንጻ ‹ለሪፎርሚስት ቢሮክራቶች› በቢሮነት እንዲያገለግል እየተሸነሸነ በመታደል ላይ ነው" የሚል ጩኸት ይደመጣል። መሃል ከተማችን ላይ ገዝፎ የሚገኘው ታላቅ ታሪካዊ ቅርስ "ምን ፋይዳ አለው" በማለት የሚያክፋፉ "ውሎ ገቦች" በገሶና በአካፋ ካላፈረስን እያሉ ለያዥ ለገራዥ ማስተቸገራቸው ያልመሸበት የትናንት ትዝታችን ነው። በታሪክ ስም ታሪክን ለማምከን የሚጥሩ፣ በእውነት ስም እውነትን ለመስቀል እንቅልፍ የሚያጡ ፀረ ቅርስ ዜጎች መገኛቸው የትም መሆኑን በርካታ አጋጣሚዎችንና አካባቢዎችን በመጥቀስ ማስታወስ ይቻላል።

የተለጠጠውን ትዝብታችንን ትንሽ ሰብሰብ አድርገን "ትዝታ አያረጅም" እንዲሉ አንድ ነጠላ ጉዳይን ብቻ መዘን እናስታውስ። በቀዳሚዎቹ ዘመናት እንደ ባህል ተቆጥሮ በበርካታ መንግሥታዊ ተቋማትና የኃላፊዎች ቢሮ ውስጥ የአገራችን ታላላቅ ሠዓሊያን የጥብብ ስራዎች በየግድግዳዎች ላይ ተሰቅለው ታሪክና ውበትን እንዲያሳዩ ይደረግ እንደነበር ዕድሜውን ያደለን ዜጎች ምስክሮች ነን።

ዓመታቱ ቢርቅም አንድ ጉዳይ እናስታውስ። በዛሬው የፓርላማ ሕንጻ የፊት ለፊት ገጽ ላይ የሦስትዮሽ ሥዕሎች (በሞዛይክ ጥበብ የተከሸኑ ሳይሆኑ አይቀሩም(?)" ተደርድረው አላፊ አግዳሚውን ይማርኩ እንደነበር ጸሐፊውን መሰል ለታሪኩ ምስክር የሆኑ ዜጎች የሚዘነጉት አይደለም። በፓርላማው የውስጠኛው ክፍሎች ደግሞ አገኘሁ እንግዳና እምአእላፍ ኀሩይን የመሳሰሉ የዘመኑ ጠቢባን የተራቀቁባቸው ሥዕሎች በየግድግዳው ላይ በክብር ተሰቅለው ስሜትን በሀሴት ያረሰርሱ ነበር።

ይህ ጸሐፊም በታዳጊነት የዕድሜ ዘመኑ ይማርበት ከነበረው የቀድሞ አራት ኪሎ ወወክማ ከብጤዎቹ ታዳጊዎች ጋር ፕሮግራም እየተመቻቸ ያንን የንጉሡ ነገሥቱን ግዙፍ የወንበረተኞች መንበር ደጋግሞ ለመጎብኘት ዕድል አጋጥሞት ስለነበር ዛሬም ድረስ ትዝታው ከአእምሮው ሊደበዝዝ አልቻለም። የደርግ መንግሥት ገና ሥልጣን ላይ እንደተቆናጠጠ ፈጥኖ የወሰደው እርምጃ እኒህን መሰል የታሪክ ምስክሮችን ማጥፋት ነበር። ታሪክ ፍርድ አሰጣጡን ያውቅበታልና ዳኝነቱን ከእርሱ እንጠብቃለን። እንዲያም ቢሆን ግን እነዚያ ክቡር የታሪክ ማስታወሻ ሥዕሎች የት እንደወደቁ ዛሬ ላይ ቆመን ብንጠይቅ ረፈዶባችኋል አሰኝቶ በይርጋ ሊዘጋ አይገባውም።

የሥዕልን ነገር ካነሳን ዘንድ ለዚህ ጽሑፍ መቆስቆሻ የሆነውን የሰሞኑን አንድ ክስተት እግረ መንገድ እናስታውስ። በሠንጋ ተራ አካባቢ በሚገኘው የቀድሞው የሞርጌጅ ባንክ፤ ዛሬ ብሔራዊ ባንክ በወረሰው ሕንጻ ወደ ውስጥ ሲዘለቅ የታላቁ የሥዕል ባለሙያ የገብረ ክርስቶስ ደስታ ገጸ ምድር (ላንድ ስኬፕ) ሥዕል በግዙፉ ግርግዳ ላይ ጏ ብሎ ተዘርግቶ የአላፊ አግዳሚውን ቀልብ፣ መንፈስና ስሜት በመማረክ የደስታ ምክንያት ሆኖ ከግማሽ ክፍል ዘመን በላይ እንደኖረ የሚያውቁ ያውቁታል። መኖሪያ ቤት ለመገንባትና የባንኩን ቢሮክራቶች ደጅ ለመጥናት ይመላለሱ ለነበሩ "ደም የለሽ ቤተ ሠሪዎች" ያ ሥዕል የስሜት መረጋጋት ይሰጥ እንደነበር ጎጂቻችንን በባንኩ ብድር ያዋቀርን በርካታ ዜጎች የምንዘነጋው አይደለም።

እንዳለመታደል ሆኖ ከሰሞኑ ያን የመሰለ የሥዕል ጥበብ ያረፈበት ግርግዳ በፓርቲሽን እየተከፋፈለ ለቢሮ አገልግሎት እንዲውል መደረጉን ያስተዋልነው እምባና ሣግ እየተናነቀን ነው። ያንን በመሰለ ግዙፍ ሕንጻ ላይ ቦታ ሳይጠብ ለምን ያ ድንቅ የጥብብ ሥራ እንዲረክስ እንደተደረገ በእውነቱ ምክንያቱ ግልጽ አይደለም። ይህንን የልብ ሀዘን በፎቶግራፍ አስደግፌ የላክሁለት አንጋፋው የሥዕል ጠቢብ ወዳጄ እሸቱ ጥሩነህ "ጥበብ ምን ተዳቸው" የሆኑ የተቋሙ ኃላፊዎች የፈጸሙትን ይህንን መሰል ግዙፍ ስህተት ከተመለከተ በኋላ በግሉ የፌስ ቡክ ገጽ ላይ የሰጠው አስተያየት እንዲህ የሚል ነው።

"አኹንም በሕግ አምላክ! በጥበብ አምላክ! ጸረ የጥበብ ቅርስ በተለይም የሥዕል ጥበባት አጥፊዎችና አውዳሚዎች እንደ ተስቦ በሽታ!...የዛሬ ሃምሳ ዓመት በሞርጌጅ ባንክ የእንግዳ መቀበያና ማረፊያ አዳራሽ ውስጥ በሠዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታ የተሣለውና የተቀባው ኪነ ግድግዳ ሥዕል (Monumental Art) [እንዳልነበረ ሆኗል]። ... ኪነ ግድግዳ ሥዕሉን ያሠራው ልበ ብርሃኑ የቀድሞ ሥራ አስኪያጅ ነው። [ምን ያደርጋል?] ከሃምሳ ዓመት በኋላ የሚመጣውን ልበ ጨለማ የባንክ ትውልድን አለማወቁ ነው! በሕይወት ካለ እንዴት ይቆጨው... ሌላው ቢቀር በዘመኑ በስንት ብር ተሰራ? ከዚያም የሥዕሉ ዕድሜ የሚያስገኘው እሴት! አልፎም ቅርስነቱ ያውም የሠዓሊ ገብረ ክርስቶስ ሥዕል ነው መባሉ ብቻ ምን ያህል ባንኩን ባኮራው ነበር።"

አገራዊ ውበትንና ታሪክን አጣምሮ የያዘ የጥበብ ቅርስ የሚመሰለው በዘር እህል ነው። የዘር እህል አይበላም። የዘር እህል የሚቀመጠው በጥንቃቄ ነው። በክፉ ዘመን እንኳን ቢሆን "መቼም አላለኝ ከዘሩ ቁይልኝ" እንዳለው ምስኪን አርሶ አደር ለጊዜያዊ ፍጆታ አይውልም። ለምን ቢሉ ቅርስ በትውልዶች መካከል መታሰቢያ ሆኖ የሚቆም ምስክር እንጂ የመጣና የሄደው ሁሉ የሚቆነጥረው፣ የጠገበ አሌ እየተነሳ ዱላ የሚያሳርፍበት ወይንም ለጊዜያዊ ጥቅም ማርኪያ አልፎ የሚሰጥ "የመስዋእት በግ" ይሉት ብጤ አይደለም። ለጋራ አገራዊ የጥበብ ሀብት ተቆርቋሪ ሆነን የምንጮኸው ጩኸት እንደሚደመጥ ተስፋ እናደርጋለን።

አሳፋሪው የባንኩ እርምጃ አሳስቦት ይህ ጸሐፊ ሰባ አምስት ዓመቱን ሊያከብር ሽር ጉድ ማለት ወደጀመረው የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የሥራ ኃላፊ ወዳጁ ዘንድ ስልክ ደውሎ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነው። በቅርቡ በህልፈተ ሕይወት ከተለዩን ዐሥር ዓመት የሆናቸው የታላቁ የጥበብ ሰው የሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ እጅግ አስደናቂ ሥዕል በዚያ አንጋፋ ሆስፒታል ዋና ግድግዳ ላይ ተንጣሎ እንደሚገኝ ይህ ጸሐፊ በሚገባ ያውቅ ስለነበረ ምናልባትም ያም ሥዕል "የሞርጌጅ" ባንኩ ጓደኛው ዕጣ ደርሶት ይሆን ወይ ብሎ በመጠራጠሩ ነበር። ምሥጋና ለሆስፒታሉ የሥራ ኃላፊዎች ይድረስና እንኳንም ሥዕሉ ሊጎሳቆል ቀርቶ በቅርቡ በተሻለ ይዞታ እንክብካቤ ሊደረግለት እንደታሰበ ተጠቁሜያለሁ። እንደነገሩኝ የሚሆን ከሆነ በርግጥም የአልማዝ ኢዮቤልዩ በዓሉ ሲከበር በቦታው ተገኝተን እናመሰግናለን።

ጎሊናችን የሚመሰክርልንን አንድ እውነታ እናስታውስ። አሁን እያስተዳደሩን ያሉት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) ከአብዛኞቹ ቀደምት መሪዎች ስሜታቸው ለጥበብ ቅርብ እንደሆነ ባንመሰክር አደራ በል እንሆናለን። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን በያዙ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያ ሥራቸው ካደረጓቸው ተግባራት መካከል አንዱ የእንጦጦን የሥዕል ጋላሪ ማሰራታቸው ነው።

ቢያንስ ለዚህ ታላቅ ተግባራቸው፣ አብርሆትን ያህል ግዙፍና ዘመናዊ ቤተ መጻሕፍት በአራት ኪሎ እምብርት ላይ ማቆማቸውና ለመጀመሪያ ጊዜ "ኢትዮጵያ ታመሰግናችኋለች" በማለት ከየጥበብ ዘርፉ በተመረጡ ጎምቱ ባለሙያዎች አንገት ላይ የወርቅ ሜዳሊያ በማጥለቅ ማክበራቸው እጅግ የሚያስመሰግናቸው ነው። በአንጻሩ "ጥበብን ለማርከስ" የሚዳፈሩ ሹመኞቻቸው የሚሰሯቸውን የማፍረስ ተልዕኮ በቅርበት እየተከታተሉ ቢገሯቸውና ቢያርቋቸው ጫጫታው ሊቀንስ ስለሚችል አደራችንን እንዲቀበሉ መልእክታችን ይድረስ እንላለን። ሰላም ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# ገበያን በማረጋጋት የህብረት ሥራ ማህበራት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት ምክንያት ምንም ይሁን ምን የምርትና የፍላጎት መጠን አለመጣጣም ግን ዋነኛ ምክንያት ለመሆኑ ምስክር አያሻውም። የአቅርቦት እጥረት ካጋጠመ ምንግዜም ቢሆን የዋጋ ንረት እንደሚከሰት ይታመናል። በአገሪቱም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በምርት አቅርቦት እጥረት እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠረው የዋጋ ንረት ከዜጎች አቅም በላይ እንደሆነና መቋቋም ያልቻሉት ጉዳይ እንደሆነ ሲያነሱ ይደመጣል።

መንግሥትም አልቀመስ ያለውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት በሚል የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል። መንግሥት ከወሰዳቸው አማራጮች መካከል የህብረት ሥራ ማህበራትን በመጠቀም የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ከደላላ ውጭ በሆነ መንገድ ለሸማቹ ተደራሽ ማድረግ አንዱ ነው። ምክንያቱም ከመሰረታዊ ችግሮች በተጨማሪ ደላሎች በአምራቹና በነጋዴው መካከል ሆነው የሚፈጥሩት ረብሻ ለዋጋ ንረቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከታቸው ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አማካኝነት የተጀመረው የእሁድ ገበያ የዋጋ ንረትን ለማርገብ ብሎም ገበያን ለማረጋጋት ጉልህ ድርሻ እየተጫወተ ይገኛል። ወራት ያስቆጠረው የእሁድ ገበያ ሲጀመረ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የማህበረሰብ ክፍል በሚኖርበት አካባቢ ከአስር በማይበልጡ ቦታዎች ሲሆን በአሁን ወቅት የክልል ከተሞችን ሳይጨምር በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ 50 በሚደርሱ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ በቋሚነት ግብይት ይካሄዳል።

የእሁድ ገበያ ከሚከናወንበት አካባቢዎች አንዱ ጀሞ አንዱ ነው። በጀሞ አንድ አካባቢ የተጀመረው የእሁድ ገበያ በስፋት ተጠናክሮ መቀጠል የቻለና ሸማቹም ከዚሁ ገበያ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። ወይዘሮ አበራሽ በቀለ በስፍራው ሲገበያዩ ካገኘናቸው ሸማቾች መካከል ናቸው። የእሁድ ገበያ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ በየጊዜው መገበያየት እንደቻሉና ከሱቅ ከሚገዙበት ዋጋ በተሻለ መጠን ቅናሽ እንደሆነና ለመኖሪያ ቤታቸውም ቅርብ መሆኑ እንደልባቸው የፈለጉትን በፈለጉ ሰዓት ወጣ ብለው እየሸመቱ መሆናቸውን ይናገራሉ።

ሌላኛው ስሜ ይቅር ያሉ ሸማች የእሁድ ገበያ በተለይም ለአትክልትና ፍራፍሬ የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ሀሳባቸውን አጋርተውናል። ለአብነትም ሙዝ በአትክልት መሸጫ ሱቅ ውስጥ በኪሎ እስከ 40 ብር የሚሸጥ መሆኑን አንስተው በእሁድ ገበያ ግን ከ25 ብር ጀምሮ የሚሸጥ መሆኑን ተናግረዋል። አያይዘውም ገበያው ውስጥ የተለያዩ ችግሮች የሚስተዋሉ መሆኑን ጠቅሰው፤ ነጋዴዎች ከህብረት ሥራ ማህበራቱ በብዛት ወስደው አትርፈው የሚሸጡ መሆኑንና ይህም ተገቢነት እንደሌለው ጠቁመዋል።

እኛም ተዘዋውረን መመልከት እንደቻልነው የእህል ዘርን ጨምሮ የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎች በብዛት ለገበያ ቀርበዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሸማችም በወረፋ ተሰልፎና ሰልፉን ጠብቆ ይገበያያል። ለአብነትም ጤፍ በኪሎ ከ44 ብር ጀምሮ በየደረጃው ቀርቧል። ስንዴ፣ ገብስና ሌሎች ጥራጥሬዎችም በገበያው አይን ሞልተው ይታያሉ። ምስር ክክ በሌላው የገበያ ስፍራ እስከ 130 ብር የሚሸጠው በእሁድ ገበያ ላይ ከ96 ብር ጀምሮ ይገኛል።

ከግብርና ምርቶች በተጨማሪም የኢንዱስትሪ ምርቶች የዳቦ ዱቄትን ጨምሮ ፓስታ፣ መኮረኒ እንዲሁም የጽዳት ዕቃዎች ሁሉም በገበያው የቀረበ ሲሆን እያንዳንዱ ዋጋም ከመደበኛው ሱቅ ዋጋ መጠነኛ ቅናሽ የሚታይበት ገበያ ሆኖ ተመልክተናል። ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም በእሁድ ገበያ የነበረው ዋጋ ላይ መጠነኛ ጭማሪ ቢታይም የግብርናውም ሆነ የኢንዱስትሪ ምርቶች ከመደበኛው የሱቅ ዋጋ መጠነኛ ቅናሽ የታየበት ገበያ ነው።

ለዋጋ ንረቱ መባባስ የምርትና የአቅርቦት አለመጣጣም እንደመሆኑ በተለይም በበዓላት ወቅት ምርት በከፍተኛ መጠን የሚፈለግ በመሆኑ በእሁድ ገበያውም መጠነኛ ጭማሪ ማሳየቱን ሸማቾች አንስተው፤ ይሁንና የእሁድ ገበያውን ጨምሮ ለበዓል የተከፈቱ ባዛሮች ገበያውን ለማረጋጋት እንደሚጠቅሙ ይገልጻሉ።

መሰረታዊ ከሆነው የምርት አቅርቦት እጥረት በተጨማሪ የግብይት ሥርዓቱ ጤናማ እንዳይሆን ጉልህ ድርሻ ያላቸው ህገወጥ ደላሎችና ስግብግብ ነጋዴዎችን ለመቆጣጠር መንግሥት ከህብረተሰቡ ጋር በጋራ መሥራት እንዳለበትም አጽንኦት ሰጥተዋል። በተለይም ወቅቱ በዓል እንደመሆኑ ለበዓል የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን መንግሥት በተመጣጣኝ ዋጋ ቢያቀርብ የተሻለ ነው። በተለይም የሥጋ ዋጋ ከአቅም በላይ በመሆኑ በህብረት ሥራ ማህበራት ሥር ያሉ ሥጋ ቤቶች ጥራት ያለውን ሥጋ በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ማቅረብ ቢችል መልካም ነው በማለት ሃሳባቸውን ቋጭተዋል።



በአዲስ አበባ የእሁድ ገበያ በ50 ቦታዎች ላይ ለሸማቶች በተመጣጣኝ ዋጋ የኢንዱስትሪና የግብርና ምርቶች ቀርቧል፤

ወቅቱ ሁለት ተከታታይ በዓላት የሚስተናገዱበት ከመሆኑም ባለፈ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ እንዲሁም ወተትና የወተት ተዋጽኦ በስፋት የሚፈለግበት በዓል ነው። በቀዳሚነት የሚከበረው የክርስትና ዕምነት ተከታዮች የሚያከብሩት የፋሲካ በዓል ሲሆን ቀጥሎ የሚከበረውም በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረው የኢድአልፈጥር ማለትም ከረመዳን የጾም ወቅት በኋላ የሚከበር በዓል ነው።

ቀድሞውኑ አልቀመስ ያለው የኑሮ ውድነት ታድያ በእነዚህ ተደራራቢ የበዓላት ወቅት ይበልጥ ተባብሶ እንዳይቀጥልና ሸማቹ ይበልጥ እንዳይማረር ምን አይነት ሥራዎች ተሰርተዋል ስንል ላነሳነው ጥያቄ በኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ወይዘሮ አያልሰው ወርቅነህ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሁለት ታላላቅ በዓላት ከፊት ለፊታችን የሚከበሩ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለዚህም የህብረት ሥራ ማህበራት ኮሚሽን የተለያዩ ዝግጅቶችን አድርጓል። በተለይም ህብረተሰቡ ዕለት ዕለት ለምግብ የሚጠቀምባቸውን የግብርና እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ማህበረሰብ ለማቅረብ ጥረት እየተደረገ ነው። በተለይም ሰፊ ህዝብ በሚኖርበት አዲስ አበባ ከተማ ላይ የህብረት ሥራ ማህበራት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በንቃት በመሳተፍ ገበያውን የማረጋጋት ሚናቸውን እየተወጡ እንደሆነ ዳይሬክተሯ ጠቅሰዋል።

የህብረት ሥራ ማህበራቱ በተለይም በመደበኛ የመሸጫ ሱቆቻቸው ላይ ከመንግሥት በተመቻቸላቸው ብድር አማካኝነት እንደ ጤፍ፣ ስንዴና ሌሎች የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረቡ ይገኛሉ። ለአብነትም የጤፍ ዋጋ ልዩነትን ብንመለከት በኩንታል ከ500 ብር እስከ 800 ብር ባለው ልዩነት አለው። ሌሎች ምርቶች ላይም እንዲሁ ከመደበኛው የሱቅ ገበያ ተመጣጣኝ የሆነ ቅናሽ በማድረግ ለህብረተሰቡ የተለያዩ ምርቶችን እያቀረቡ ነው።

ህብረት ሥራ ማህበራቱ በመደበኛነት ከሚያቀርቡት ምርቶቻቸው በተጨማሪ መጪዎቹን ሁለት በዓላት አስመልክተው እንደ አትክልትና ፍራፍሬ በተለይም ሽንኩርት እንዲሁም ለበዓሉ አስፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ወተትና የወተት ተዋጽኦዎችን ለአብነትም ቅቤ፣ አይብና ሌሎችንም ይዘው ቀርበዋል። በተጨማሪም ዶሮና የዶሮ ተዋጽኦ የሆነውን እንቁላል ወደ ገበያው በማቅረብ ሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ እያቀረቡ ሲሆን፤ ከእነዚህ በተጨማሪም በዓሉ በዋናነት ሥጋና የሥጋ ውጤቶች የሚፈለጉበት እንደመሆኑ የሥጋ ከብቶችን ከአምራች የህብረት ሥራ ማህበራቱ ጋር በመተሳሰር በቀጥታ ባሉት የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት ማዕከል ለማቅረብ የሥጋ ከብት ግዢ እየተከናወነ ይገኛል።

**የህብረት ሥራ ማህበራቱ በዋናነት የግብርና ምርቶች የሆኑትን እንደ ጤፍ፣ የስንዴ ዱቄትና ሌሎችንም ህብረተሰቡ ዕለት ተዕለት የሚጠቀማቸውን ምርቶች ለገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ**

ወቅቱ የበዓል እንደመሆኑና ሰፊ ግብይት የሚካሄድ እንደመሆኑ የህብረት ሥራ ማህበራቱ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት እንዲችል የተሰራ ሥራ መኖሩን የጠቀሱት ዳይሬክተሯ፤ በተለይም በመደበኛ የህብረት ሥራ ማህበራት ሱቆች ላይ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ቀደም ብለው የመሸጫ ሱቆችን እንዲከፍቱና ዘግይተውም እንዲዘጉና አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅትም እንዲሁ ቀልጣፋና ጥሩ የሚባል አገልግሎት እንዲሰጡ የማስቻል ሥራ ተሰርቷል።

በእሁድ ገበያም እንዲሁ ህብረተሰቡ ጋር ተደራሽ ለመሆን የህብረት ሥራ ማህበራቱ በስፋት እየተንቀሳቀሱ ሲሆን የመሸጫ ቦታዎችንም ከጊዜ ወደ ጊዜ በማስፋት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ 50 በሚደርሱ ቦታዎች ላይ ሽያጭ ይካሄዳል። ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ባሉ የክልል ከተሞችም እንዲሁ የእሁድ ገበያው ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን በተለይም ሰፊ ህዝብ በሚኖርባቸው ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር፣ በደቡብ ክልል የተለያዩ ከተሞች፣ ሀረርና በሌሎችም ከተሞች ተጀምሯል። በዚሁ የእሁድ ገበያ አምራች የህብረት ሥራ ማህበራት በቀጥታ ከሸማቹ ጋር ተገናኝተው የተለያዩ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶቻቸውን መገበያየት እንዲችሉ በማድረግ ገበያውን በማረጋጋት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

ይሁንና የምርት ዋጋ ተማኝ አርሶ አደሩ ባለመሆኑ በየቀኑ የዋጋ መቀያየር መኖሩን ያነሱት ዳይሬክተሯ፤ የዋጋ ተማኝ የሆነውን አካል በመቆጣጠር ወደ ህጋዊ የንግድ ስርዓት ለማስገባት የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ርብርብ ማድረግ ይገባቸዋል። ይህንን ጤናማ ያልሆነ የግብይት ሥርዓት መስመር ማስያዝ ካልተቻለ በንግድ ሥርዓቱ ላይ ያለውን ችግር በዘላቂነት መፍታት አይቻልም ብለዋል።

አሁን ባለው የገበያ ሁኔታ ከየትኛውም ነጋዴ በተሻለ የህብረት ሥራ ማህበራቱ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ እያቀረቡ ይገኛሉ። ለዚህም ዋናው ምክንያት የግብይት ሰንሰለቱን ማሳጠር በመቻላቸውና በቀጥታ ሸማቹን ማግኘት ስለሚቻል ሲሆን ሁለኛው ደግሞ ማህበራቱ ለትርፍ የተቋቋሙ ሳይሆኑ ህብረተሰቡን ለማገልገል የቆሙ በመሆናቸው ጭምር ነው። በመሆኑም ከፍተኛ የሆነ የትርፍ ህዳግ ሳይዙ ማህበረሰቡን የሚያገለግሉ ናቸው።

የህብረት ሥራ ማህበራቱ በዋናነት የግብርና ምርቶች የሆኑትን እንደ ጤፍ፣ የስንዴ ዱቄትና ሌሎችንም ህብረተሰቡ ዕለት ተዕለት የሚጠቀማቸውን ምርቶች ለገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ። በተለይም በአሁን ወቅት ለበዓሉ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ዶሮዎችን፣ እንቁላል፣ የወተት ተዋጽኦዎችን እና የቁም እንስሳትን የሆኑትን የበሬ ሰንጋዎች እያስገቡ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች ለበዓሉ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን እያቀረቡ ናቸው።

በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ 50 በሚደርሱ የተለያዩ አካባቢዎች የእሁድ ገበያ የሚቆም ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ወጪ የሚወጣበት መሆኑን የጠቀሱት ዳይሬክተሯ፤ አዋጭነት ኖሮት ሳይሆን ህብረተሰቡን ለማገልገል ታስቦ እንደሆነ አንስተዋል። ይህንኑ ገበያ ከእሁድ ውጪ በየዕለቱ ለማድረግም አዋጭ አይደለም ብለዋል። ይህም ለህብረተሰቡ ትልቅ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ያሳያል።

እስካሁን በነበረው ሂደት ህብረት ሥራ ማህበራቱ በተወሰኑ ምርቶች ላይ ተገድቦ ብድር የሚሰጣቸው መሆኑ እንደችግር ይነሳል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ከገደብ ውጭ ሆኖ አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ምርቶችን ወቅቱ እንደሚጠይቀው መግዛትና ማቅረብ እንድንችል የሚል ጥያቄ አላቸው። ከዚህ ውጭ ደግሞ በተለይም የእሁድ ገበያ በተመቻቸ ሁኔታ ላይ የሚሰራ ሥራ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ የደህንነትና የምቾች ጥያቄዎች ይነሳሉ።

እነዚህን ችግሮች ግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊ የሆኑ የመሰረተ ልማቶች በማሟላት ደረጃቸውን የጠበቁ የገበያ ቦታዎችን ለህብረተሰቡ ቅርብ የሆነና ምቾት ያላቸውን የገበያ ማዕከላትን ለመገንባት የሚችልበትን ሥርዓት ለመዘርጋት የዲዛይንና የቦታ መረጣ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ይህ ሥራ ሲጠናቀቅም እጅግ ዘመናዊና ምቹ የሆኑ የገበያ ማዕከላት በተለያዩ የከተማ አካባቢዎች ላይ ማየት ይቻላል።

በአሁን ወቅት በአገሪቱ ያለው የገበያ ሥርዓት አምራቹም ሆነ ሸማቹ ተጠቃሚ ያልሆነበት ሥርዓት መሆኑን ያነሱት ዳይሬክተሯ፤ ለዚህም ዋናው ምክንያት አጠቃላይ የገበያ ሥርዓቱ ብልሽት ሲሆን ይህም በህብረት ሥራ ኮሚሽን ብቻ የሚፈታ ችግር አይደለም። ይሁንና ይህን ለማስተካከል ኮሚሽኑ በህብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት የተለያዩ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ከአምራቹ በቀጥታ ወደ ሸማቹ መድረስ የሚችልበትን ሥራ እየሰራ ይገኛል። በቀጣይም ምርትን አምራቹ በሚሸጥበት ዋጋ ለተጠቃሚው መድረስ እንዲችል በመሀል ያለውን ሰንሰለት የማቋረጥ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል። ለዚህም በርካታ ባለድርሻ አካላት ያሉ ሲሆን ከእነሱ ጋር በመቀናጀት የሚሰራ ይሆናል።

በመጨረሻም ህብረተሰቡ ተባብሶ የቀጠለውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት ትልቅ አቅም ያላቸውንና ህብረተሰቡ ራሱ ያቋቋማቸውን የህብረት ሥራ ማህበራት በባለቤትነት ደግፎ ተጠቃሚ የሚሆንበት መንገድ በቅርብ ሆኖ እንዲደግፍ ዳይሬክተሯ ጥሪ አቅርበዋል። ተቋማቱ በሁለት እግራቸው ቆመው ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ ጠጋ ብሎ ምን አይነት ምርቶች ቀርበዋል? ምንስ ችግር አለ ? ብሎ በመጠየቅ ያቋቋማቸውን ህብረት ሥራ ማህበራት እንዲደግፍና ተጠቃሚ እንዲሆን ሲሉ ጥሪ አስተላልፈዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የመብላት አገልግሎት!

**ይቢ ከደጃች. ውቤ**

በአንድ የሸገር መንደር መብራት ከጠፋ ወደ አንድ ሳምንት ሆነው፤ ልጆች ከትምህርት ቤት መልስ ለማጥናትና የቤት ሥራ ለመሥራት ተቸገሩ። ወላጆች በቀላሉ ምግብ የሚሠሩበትና የሚያበስሉበት አጡ። የበሰሉ ምግቦችን ለመግዛትና አንዳንዴም ወደ ሁዋላ ተመልሰው በከሰልና በእንጨት ማገዶ ለማብሰል ተገደዱ። በእዚህ አይነት ሁኔታ ጉድጉድ ሲሉ ልጆች ደግሞ ምግቡ ቶሎ እንዲደርስ በዙሪያቸው ሲንቀሳቀሱ ክፉ ጊዜ የመጣባቸው መሰለ።

በምሽት አባወራ ዜና ለመስማት ኮረዶችና ጉብሎችም በድራማ በዘፈንና ስፖርት ዘና ለማለት የሚያስቡበት ቴሌቪዥን መብራት ስለሌለ ጥቁር ሰሌዳ መሰለ። እሱም በሻማ፣ በባትሪ፣ በሶላር መብራት ነው የሚታየው።

የቴሌቪዥን ፕሮግራም መጥፋቱ ግራ የገባው ህፃን ልጅ «ማሚ መብላት ዛሬም አታመጪም?» ሲል በኮልታፋ አንደበቱ መጠየቁን ሰዎች ሲናገሩ ሰምቻለሁ። ብላቴናው አንደበቱ መብላት ያለው መብራትን ነው።

ይህን ዘገባ ለመጻፍ የተነሳሳሁት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መብራት ጠፍቶባቸው አስር ቀናት የሆናቸው ሰዎች ለዚህ ጋዜጣ ያቀረቡትን ቅሬታ በዜና አንብቤ ነው። የሚገርመው ግን ዜናው ከተዘገበም በኋላ የአገልግሎቱ ሰራተኞች ለተጨማሪ አምስት ቀናት ኤሌክትሪክ ለመቀጠል ሰዎቹን ሲያጉላሉ ነው የሰነበቱት።

ምን ይህ ብቻ። ሰሞኑን በአዲስ አበባ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሶስት ባለሙያዎች የአንድ ግለሰብን የኤሌክትሪክ መስመር ከቆጣሪው ቆርጠው ሃይል በማቋረጥ መልሶ ለመቀጠል ጉቦ ጠይቀው ሲቀበሉ እጅ ከፍንጅ መያዛቸውን የአዲስ አበባ ፖሊስ ገልጧል። ወንጀሉ የተፈፀመው በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ልዩ ቦታው ጨው በረንዳ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ሲሆን፣ ተበዳይ ነው ለፖሊስ አመልክቶ ብሩን ሲሰጥና ሲቀበሉ እጅ ከፍንጅ ያስያዛቸው። ጎበዝ! እነዚህ ቀበኞች አደብ ለማስገዛት እንዲህ አይነት ብርቱዎች ያስፈልጉናል። ለዚህ ዘገባ መጻፍ ይህም ሌላው ምክንያቴ ነው።

ጉቦ ለመጠየቅ በሚል ሆን ብሎ የኤሌክትሪክ መስመር መቁረጥ ትልቅ ወንጀል ነው። እነዚህ ተጠርጣሪዎች ተያዙ እንጂ ይህን መሰሉ ድርጊት በስፋት እየተፈጸመ ስለመሆኑ ህብረተሰቡ ሲገልጽ ይሰማል።

የኤሌክትሪክ ሀይል ለከተማ ነዋሪዎች መብራት ብቻ አይደለም፤ ራትም ነው። ገቢው የሚገኘው አንድም በመብራት ነው። ዛሬ ዛሬ ደግሞ ወጪ ለማድረግም መብራት ያስፈልጋል። ይህን ሁሉ ታሳቢ በማድረግ አገልግሎቱ ለአፍታም መቋረጥ የሌለበት ቢሆንም፣ በአገራችን ግን ለአፍታ አይደለም ለቀናት ለሳምንት ለሳምንታትም ይጠፋል። የአንድ ቤት መብራት ብቻ ሳይሆን የመንደር መብራት ጭምር ለረጅም ጊዜ ይጠፋል። ይህ ሲሆን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሲበርደውም ሲሞቀውም አይስተዋልም።

አንደ አገር፣ አንደ አካባቢ በኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ላይ በተፈጠረ ችግር አገልግሎቱ ቢቋረጥ አይደንቅም። በተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች ቢጠፋና መመለስ የሚቻልበት እድሉ እያለ ጉቦ ካልተከፈለ/ በእነሱ አጠራር /የሻይ ካልተባለ/ የማይመለስበት ሁኔታ ግን በእጅጉ ያነጋግራል። አንዳንድ የአገልግሎቱ ሰራተኞች የተቋረጠ የኤሌክትሪክ ሀይል እንዲቀጠል በሃላፊዎቻቸው እየተነገራቸውም ፈጥነው አይፈጽሙም፤ ለእዚህም ጉቦ ይፈልጋሉ። ይህን የተመለከቱ ቅሬታዎችን ከህብረተሰቡም ከመገናኛ ብዙሃንም ነጋ ጠባ በስፋት ማዳመጥ ተለምዷል።

ቆጣሪ ያልቆጠረውን ሂሳብም ክፍሉ ብሎ መጠየቅ፣ የማይከፍሉ ከሆነ መብራቱን እንቆርጠዋለን እያሉ ማስፈራራትም አለ። የባሰ አታምጣ። አንድ እማወራ ልጃቸውን ትምህርት ቤት ከላኩ በኋላ የመንግሥት ሠራተኛ በመሆናቸው ለሥራ ይገባሉ። ጎረቤታቸውም ከባለቤታቸው ጋር ለግል ሥራ ስለሚሄዱ ግቢው ዝግ ይሆናል። ቆጣሪ አንባቢው መጥቶ ግቢው ዝግ መሆኑን አይቶ በመላምት የአገልግሎት ክፍያውን ቆጣሪውን ሳያይ መዝግቦ ይሄዳል። የመብራት የአገልግሎት ሂሳቡ ሲመጣ ሁለቱም በአንድ ቆጣሪ የሚጠቀሙ ተከራዮች 3 ሺህ 800 ብር እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ።

እነዚህ ሰዎች የሂሳቡ መብዛት አሳሰባቸው፤ ግራ ገባቸው፤ በየወሩ ከአንድ ሺህ 500 የዘለለ ከፍለው አያውቁም። በቃ እንከፍላለና እንደፈረደብን ምን እናደርጋለን ሲሉ፤ አንደኛው ሄጂ ቆጣሪው ይመርመርልኝ ክፍያው በዛብኝ እላለሁ አሉ። እንዳሉትም ኤሌክትሪክ ኃይል ሄደውም አስረዱ፤ ኃላፊው ቀና ስለነበሩ፤ ጉዳዩን አይተው የቆጠረውን ጠርተው ጠይቀው ሁለተኛ በመላምት እንዳይሠራ ጭምር አስጠንቅቀው ሸኙት። የተገልጋዩ የክፍያ ሂሳብ ሲታይ ግን 1ሺህ 400 ብር ነበር፤ ይህም ተነግሯቸው ከፈሉ።

በዚህ ላይ የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ትልቁ ችግር ነው። ይህ አንደ አገር ያለ ችግር ሊሆን ይችላል። አንድ መንደር ከተማ ላይ ሲጠፋ ሌላ ምንም ስለማይባል። ሁኔታው ግን ለኪራይ ሰብሳቢዎቹ ሰርግና ምላሻቸው ነው። የሚፈልጉትን ጉርሻ ለማግኘት ብለው ቶሎ መልቀቅ የሚችሉትን መብራት ያቆዩታል።

ያሉበት ህፀፆች ተዘርዝረው አያልቁም። መብራት ሲቋረጥ 905 በተደጋጋሚ ደውላችሁ ስልኩንም ላያነሱላችሁ፣ አንስተውም ከሆነ ላይመጡላችሁ ይችላሉ። መስሪያ ቤታቸው በአካል ስትሄዱ በቃ ሠራተኛ እንልክላችኋለን የሚለው የተለመደ ምላሻቸው ነው።

ዕድለኛ ሆናችሁ ሠራተኞቹ ከመጡ ደግሞ ብልሽቱን አይተው አንዳንዶቹ መጀመሪያ « ቀላል ነው፤ ይሰራል፤ ግን የሻይ የቡና ትሉናላችሁ» የሚል ጥያቄ ያነሳሉ። ሌሎች ደግሞ ችግሩ ብዙ ነው ብለው ማስደንገጥ ይጀምራሉ። ይህ ሁሉ የሚሆነው ጉቦ ለመቀበል ነው። ደመወዛቸውን ከመሥሪያ ቤታቸው እየተቀበሉ በተጨማሪ ከተገልጋዩ ክፍያ መጠየቅ የለመዱት ነው።

መብራት ተቋርጦባቸው ወዲያው የሚቀጠልላቸውም እንዳሉም ይሰማል። እነዚህ ደግሞ ጉቦ ሰጥተው የሚያስቀጥሉ ናቸው። ለእዚህም ነው አንዳንዶች መብራት ጠፍቶ አያያዙ አላምር ሲላቸው ገንዘብ እናዋጣ ወደሚለው ፈጥነው የሚገቡት። ጉቦ መክፈላቸው ትክክል አይደለም፤ መመላለሱን፣ ለትራንስፖርት የሚወጣውን፣ መብራት ባለመኖሩ ሳቢያ እቤት ውስጥ የሚጠፋውን ሀብት አስበን ነው ሲሉ የሰማሁዋቸው አሉ። ትክክለኛው መንገድ ግን መብታቸውን ማስከበርና ማጋለጥ ነው።

ይህን የለመዱት የአግልግሎቱ ሰራተኞች ሁሉም ደንበኛ በእዚህ መልኩ የሚከፍላቸው አርገው እስከ መገመት ደርሰዋል። ቀበኞቹ በቀላሉ ሊሰሩ የሚችሉትን ጭምር ከባድ ችግር አርገው በመንገር ገና ለቀናት ሊጠፋ እንደሚችልም በመግለጽ ህብረተሰቡ በጉቦ እንዲያስቀጥል ለማድረግ ግፊት ያሳድራሉ። ይህን ይህን የተመለከቱ ታዲያ አገልግሎቱን የመብራት አገልግሎት ከማለት ይልቅ የ«መብላት አገልግሎት» እያለ እስከ መጥራት ደርሰዋል ይባላል።

ሕዝብ ለማገልገል የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት መሥሪያ ቤት ተገልጋዩን በማጉላላትና ክፍያ በመጠየቅ ሲያንከራትት መስማት ገራሚ ነው። ይህ ችግር ከተቋሙ ጋር ቆይቷል፤ አንድ ሰሞን ችግሩን ለመፍታት እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን ሲገልጽ ነበር፤ በአንዳንድ ቦታ በካርድ መብራት የመሙላቱ ሁኔታ ትንሽ ማሻሻል አሳይቷል፤ አሁን የሚሰማው የአገልግሎት ችግር ግን መስሪያ ቤቱ እንዳልተለወጠ ያመለክታል።

በእዚህ ወቅት እነዚህን ቅሬታዎች መስማት የኤሌክትሪክ አገልግሎት አሁንም ኪራይ ሰብሳቢዎች የተሰገሰጉበት መሆኑን ያመለክታል፤ ችግሩ «ሃይ» የሚለው በማጣቱም እሮሮውም ቀጥሏል፤ የእነዚህ ቀበኞች ድርጊት የመስሪያ ቤቱን ስም በእጅጉ እያጎደፈው ነው። ቀበኞቹ ድርጅቱን የብልሹ አስተዳደር ተምሳሌት እንዲሆን ማድረጋቸውን ቀጥለውበታል።

የኤሌክትሪክ ሀይል ለአፍታም መቋረጥ በሌለበት አለም ውስጥ ነው ያለነው። የኤሌክትሪክ ሀይል ለብርሃን ብቻ አይደለም የሚፈለገው። በኪሳችን ይዘን ከምንዞረው ሞባይል አንስቶ ግዙፍ የኤሌክትሪክ ሀይል እስከሚፈልጉት ተቋማት ድረስ ያስፈልጋል። በተገልጋይ ላይ ይህን ያህል አንግልት መፈጸም፣ ጉቦ ለመቀበል ማንገላታት ከአንድ አገልጋይ መስሪያ ቤት አይጠበቅም፤ ህዝብ እንዲማረር ማድረግ ትርጉሙ ብዙ ሊሆን ስለሚችልም መስሪያ ቤቱ በመልካም አስተዳደር ላይ አተኩሮ መስራት አለበት፤ ወቅቱም ይህን ለመስራት ያመቸ ነውና ሊጠቀምበት ይገባል። በጥሩ ስም ሊጠራ ሲገባው ፤«የመብላት አገልግሎት» አገልግሎት እየተባለ መዘባበቻ መሆን አልነበረበትም። አገልግሎቱ ስሙን ማደስ ይኖርበታል።

# ዓለም አቀፍ

## የኤምሬትስ አየር መንገድ ወደ ሩሲያ መብረሩን እንደሚቀጥል ገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የኤምሬትስ አየር መንገድ ኃላፊ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ መንግሥት ክልከላ ካልጣለ በስተቀር አየር መንገዱ ወደ ሩሲያ የሚያደርገውን በረራ እንደሚቀጥል አስታወቁ።

“አቁሙ ከተባልን እናቆማለን ካልሆነ በየጊዜው የምናደርገውን በረራ እንቀጥላለን” ሲሉ ኃላፊው ሰር ቲም ክላርክ ተናግረዋል።

የዩክሬን ጦርነት መቀስቀሱን ተከትሎ ምዕራባውያን ሃገራት በርካታ ማዕቀቦችን ጥለዋል እንዲሁም ዋና ዋና የሚባሉ ዓለም አቀፍ አየር መንገዶችም ሩሲያን ለቀው ወጥተዋል።

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የኤምሬትስ አየር መንገድ ወደ ሩሲያዎቹ ሞስኮና ሴንት ፒተርስበርግ ከተሞች በረራዎችን ከሚያደርጉ ጥቂቶቹ አንዱ በመሆን ቀጥሏል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

አየር መንገዱ ይህንን አቋም እንደገና ያጤነው እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄም የአየር መንገዱ ኃላፊ የእሳቸው ውሳኔ ሳይሆን የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ መንግሥት የሚወስደው እርምጃ ነው ብለዋል።

አየር መንገዱ መንገደኞችን ከማጓጓዝ በተጨማሪ በማዕቀቡ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ የሰብአዊ ቁሳቁሶችን የምግብና የህክምና አቅርቦቶችን ጨምሮ ሌሎች ጭነቶችን ያጓጉዛል። የሩሲያ ህዝብ በዩክሬን ውስጥ ያለው ጦርነት አካል ላይሆን እንደሚችል መገንዘብ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

እናም በሞስኮ ውስጥ ተልእኮ ያላቸው ሌሎች አገራት ዲፕሎማሲያዊ ስራቸውን ወደ አገር ውስጥ በመግባት እና በመውጣት መስራት መቻል አለባቸው ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

“በምናደርጋቸው በረራዎች በዋናነት ህዝብን እያገለገልን ነው፤ ምናልባትም የዩናይትድ አረብ ኤምሬትስ መንግሥት የሚመለከተው በዚህ መንገድ ነው” ብለዋል። በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የነዳጅ ጭማሪ ቢኖርም በረራዎችም በዚሁ መጠን መጨመራቸውን ይናገራሉ።

አየር መንገዱ የነዳጅ ጭማሬውም ጋር በተያያዘ በአውሮፕላን ታሪፎች ላይ ተጨማሪ ዋጋ ቢጥልም ይህ ሁኔታ በመንገደኞችም ላይ ሆነ በጭነት አጓጓዦች ላይ ያመጣው ለውጥ የለም ይላሉ።



ሰር ቲም ክላርክ

## ባይደን በአውሮፕላን እና ባቡር ውስጥ ማስክ እንዲደረግ ያወጡትን ሕግ የአሜሪካ ፌደራል ዳኛ ውድቅ አደረጉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በፍሎሪዳ የሚገኙ አንድ የፌደራል ዳኛ የባይደን አስተዳደር አውሮፕላኖች እና ሌሎች የሕዝብ ማጓጓዣዎች ላይ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ እንዲደረግ ያወጣውን ሕግ " ሕጋዊ አይደለም" ሲሉ ውድቅ አደረጉ።

ዳኛ ካትሪን ኪምቦል ሚዜል የብሔራዊ ሕብረተሰብ ጤና ኤጀንሲ ሕጉን በማውጣት ሕጋዊ ሥልጣኑን ተላልፏል ብለዋል። የአሜሪካ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ከአሁን በኋላ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ እንደማያስገድድ አስታውቋል።

የአሜሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከል (ሲዲሲ) ባለፈው ሳምንት ሕጉን እስከ አውሮፓውያኑ ግንቦት ሦስት ድረስ አራዝሞት ነበር። ተቀማጭነታቸውን ፍሎሪዳ ያደረጉት ዳኛ ሚዜል የፌደራል ዳኞች በአገር አቀፍ ደረጃ የመንግሥት ፖሊሲዎችን የሚያግዱ



ውሳኔዎችን ሊሰጡ ይችላሉ ብለዋል።

ዳኛዋ ሰኞ ዕለት ያስተላለፉት ውሳኔ በሁሉም አየር ማረፊያዎች፣ ባቡሮች፣ ታክሲዎች እና መተላለፊያ ቦታዎች ማስክ ማድረግ የሚለውን ግዴታ እንደሚሽር ቢቢሲ ዘግቧል።

የዋይት ሃውስ ፕሬስ ሴክሬታሪ ጄን ፕሳኪ ውሳኔውን "የሚያሳዝን" ያሉት ሲሆን ሲዲሲ አሁንም መንገደኞች አፍና አፍንጫቸውን እንዲሸፍኑ እንደሚመክር ተናግረዋል። ሲዲሲ ሰኞ ዕለት በተሰጠው ብይን ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ለቀረበለት ጥያቄ ምላሽ አልሰጠም።

ባለፈው ሳምንት የአሜሪካ የኅብረተሰብ ጤና ባለሥልጣን ሰርጂን ጀነራል ቪቬክ ሙርቲ በኮቪድ-19 የሚያዙ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ እስከ ግንቦት ድረስ መራዘሙን አስታውቀው ነበር።

ክሱ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ፍርድ ቤት ያመራው ባለፈው ዓመት ሐምሌ ወር ላይ በወግ አጥባቂው ቡድን የጤና ነጻነት መከላከያ ፈንድ (ኤችኤፍዲኤፍ) እና ሁለት የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ ጭንቀታቸውን እና ድንገተኛ ድንጋጤን ይጨምራል ባሉ ሁለት የፍሎሪዳ ነዋሪዎች ነው።

ከሳሾቹ የሲዲሲ ሕግ ልክ ከሁለት ዓመት በታች እንዳሉ ህጻናት ሁሉ ለተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ነጻነትን የሰጠ በመሆኑ "ዘፈቀዳዊ እና ወጥ ያልሆነ" ሲሉ ተከራክረዋል።

በቀድሞው ፕሬዚደንት ዶናልድ ትራምፕ የተሾሙት ዳኛ ሚዜል በውሳኔው ላይ "ሥርዓታችን ፍላጎቶችን ለማስተናገድ ኤጄንሲዎች በሕገ ወጥ መንገድ እንዲሰሩ አይፈቅድም" ብለዋል።

በመሆኑም "ፍርድ ቤቱ ሕጉ ሕገ ወጥ መሆኑን በማወጅ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግን የሚያስገድደው ትዕዛዝ እንዲነሳ አድርጓል" ሲሉ ተናግረዋል።

ውሳኔው ከተላለፈ በኋላ የአሜሪካ አየር ማረፊያን ደህንነት የሚመራው የትራንስፖርት ደህንነት አስተዳደር የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ትዕዛዝን እንደማይፈፅም አረጋግጧል።

ዩናይትድ ኤርላይንስ፣ ዴልታ አየር መንገድ፣ የአላስካ አየር መንገድ እና አሜሪካን ኤርላይንስ በበኩላቸው በአገር ውስጥ በሚደረጉ በረራዎች እና በተወሰኑ የውጭ በረራዎች ላይ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ እንደማያስገድድ አስታውቀዋል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# መንገሻ ጀንበሬ - ደማቁ የኢትዮጵያ የነፃነት ጀንበር

**አንተነህ ቸሬ**

እንደ ኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር 1888 ዓ.ም፣ ዓድዋ … የቅኝ ግዛት ፍላጎቱን ለማሳካት ኢትዮጵያን የወረራው ዒላማ አድርጎ ገስግሶ የመጣው የኢጣሊያ መንግሥት/ጦር በኢትዮጵያዊያን ልዩና ታሪካዊ አንድነት በተሰጠ ምላሽ የሽንፈት ማቁን ተከናነበ። ጣሊያኖች ዓድዋ ላይ ድል ከሆኑ በኋላ ለአጭር ጊዜ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ የሚከተሉትን የመስፋፋት ፖሊሲ እንደ መግታት ብለው ነበር። ከሽንፈቱ በኋላ አዲስ የተሾመው ጠቅላይ ሚኒስትር ዲ ሩዲኒ ቀዳሚው ፍራንቸስኮ ክሪስፒ ያራምድ የነበረውን ፖሊሲ ሽሮታል፤ ለቅኝ ግዛት ማስፋፊያ የተመደበውን በጀት በግማሽ ቀነሰው፤ ከዓድዋ ጦርነት በፊት አንገቱን ደፍቶ የነበረው የፀረ-ኮሎኒያሊስት ቡድን አሁን የልብ ልብ አግኝቶ ኢጣሊያ ከነ አካቴው የአፍሪካን ምድር ለቃ እንድትወጣ ለመጠየቅ ደፈረ። ይህ ሁሉ ግን የቆየው ለአጭር ጊዜ ነበር።


ከእንግሊዝ ቀጥሎ ከኢትዮጵያ ጋር ረጅም የጋራ ድንበር ያሏቸውን ቅኝ ግዛቶች የምታስተዳድረው ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ችላ ብላ መኖር አልቻለችም። ከዓድዋ ሽንፈት 30 ዓመታት በኋላ ወደ ስልጣን የመጣው አምባገነኑ የፋሺዝም አቀንቃኝ ቤኒቶ ሙሶሊኒ፣ ራሱን እንደ ሮም የቀድሞው ንጉስ ጁሊየስ ቄሳር በመቁጠርና "የኢጣሊያን ክብር ለዓለም አሳያለሁ" በሚል የረጅም ጊዜ ተስፋ የቅኝ ግዛት ዘመቻውን ሊያሳካ ላይ ታች ማለቱን ተያያዘው። ነገሩ ይህ ብቻ አልነበረም፤ ኢጣሊያውያን በውስጥ ችግሮቻቸው ላይ የነበራቸውን ትኩረት ለማስቀየር፣ እየጨመረ ለመጣው የኢጣሊያ ሕዝብ የማስፈሪያ ቦታ ለመፈለግ እንዲሁም በአውሮፓ መድረክ የከሸፈበትን የመስፋፋት ፖሊሲ ለማካካስ ቅኝ ግዛትን አማራጭ አድርጎ ተነሳ። ከሁሉም በላይ ግን ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የተከናነበችውን ሽንፈት ለመበቀል ሙሶሊኒ ፊቱን ወደ ኢትዮጵያ አዞረ።

ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የተከናነበችውን ሽንፈት ለመበቀል ለአርባ ዓመታት ያህል ስትዘጋጅ ከኖረች በኋላ በየጊዜው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በባህል መስክ የተፈራረመቻቸውን የሰላምና የትብብር ውሎችና በመንግሥታቱ ማኅበር አባልነቷ የገባቻቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ሁሉ ‹‹ከእንግዲህ አላውቃቸውም›› አለች። ከብዙ ጊዜያት ዝግጅትና የጠብ አጫሪነት እንቅስቃሴዎች በኋላ፣ ፋሺስት ኢጣሊያ በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ወረረች።

ይሁን እንጂ መቼውንም ቢሆን በአገሩና በነፃነቱ የማይደራደረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የፋሺስትን አገዛዝ ‹‹አሜን›› ብሎ አልተቀበለውም። ይልቁንም ጨርቄን ማቄን ሳይል ‹‹ጥራኝ ዱሩ›› ብሎ ለነፃነቱ መፋለም ጀመረ። የኢትዮጵያውያን ‹‹እምቢኝ ለአገሬ! ድል ለእናት ኢትዮጵያ፤ ሽንፈትና ሞት ለኢትዮጵያ ጠላት!…›› ባይነት የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አንዲትም ቀን እንኳን እፎይ ብሎ ሳይቀመጥ ከአምስት ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ ሌላ የሽንፈት ማቅ ለብሶ ከኢትዮጵያ ምድር እንዲባረር አደረገው። ታዲያ በዚህ አስገራሚና አኩሪ የመስዋዕትነት ጉዞ ውስጥ ደማቅ የጀግንነት ታሪክ ከፃፉና ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ከተጋደሉ እልፍ የኢትዮጵያ ጀግኖች መካከል ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ አንዱ ነበሩ።

መንገሻ ጀንበሬ የተወለዱት ግንቦት 13 ቀን 1884 ዓ.ም ጎጃም ውስጥ፣ ሜጫ፣ ጉታ አውራጃ አካባቢ ነው። አባታቸው ደጃዝማች ጀንበሬ እምሩ የሜጫ፣ የዴንሳ፣ የጉታና የአገው ምድር ባላባት በመሆን ለብዙ ዓመታት አካባቢውን አስተዳድረዋል። ደጃዝማች ጀንበሬን ጨምሮ አያቶቻቸውና ቅድመ አያቶቻቸው ሁሉ የደጃዝማች ማዕረግ ነበራቸው። መንገሻ ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ብልህና አስተዋይ እንዲሁም በአልሞ ተኳሽነታቸው ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው፤ በበገና ድርደራ እና በፈረስ ግልቢያም የሚታወቁ ነበሩ። ለአደንና ለውሃ ዋናም ልዩ ፍቅር ያላቸው ጀግና ነበሩ።

መንገሻ በተወለዱ በዘጠኝ ዓመታቸው አባታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ከአያታቸው ደጃዝማች እምሩ ቤት ሆነው የቤተ ክህነት ትምህርት ተከታተሉ።



ከዚያ በኋላም አያታቸው ደጃዝማች እምሩ ሲያርፉ ከአጎታቸው ደጃዝማች ሽፈራው እምሩ ጋር በመሆን የተለያዩ ወታደራዊ ስልጠናዎችንና የአስተዳደር ስልቶችን እየተማሩ አደጉ። የመንገሻን ጀግንነትና ብልሃት የተመለከቱት አጎታቸው ደጃዝማች ሽፈራው፣ ከሚያስተዳድሩት ግዛት በመቀነስ ቆላ አቦሌ የሚባለውን ግዛት እንዲያስተዳድሩ ሾሟቸው።

መንገሻ በ32 ዓመታቸው የደጃዝማችነት ማዕረግ በማግኘታቸው የቡሬ ዳሞት አውራጃንና የሰከላ አካባቢዎችን ማስተዳደር ጀመሩ። በመልካም ፀባያቸው፣ በአስተዋይነታቸው እና ለአገራቸው ባላቸው ልዩ ክብር ምሥጉን ሆኑ። የሚያስተዳድሩት አካባቢ የፀጥታው ችግር የሌለበት፣ በሁሉም ዘንድ የሚወደድ ባሕርይ እንዳላቸው በመታወቁ ሜጫን እንዲያስተዳድሩ ትልቅ ኃላፊነት ተሰጣቸው። ደጃዝማች መንገሻ በወቅቱ እሳቸው በሚያስተዳድሩት ግዛት ውስጥ ፍርድ የሚያጓድል፣ ድሃን የሚበድል፣ መንገደኛን የሚዘርፍና በአጠቃላይ ሕገ ወጥ ተግባራትን የሚፈጽም ሰው ሲኖር በፍጥነት ፍርድ በመስጠት የሚታወቁ ነበሩ።

በ1928 ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ደጃዝማች መንገሻ በግዛታቸው ማለትም በሜጫ አውራጃ አካባቢ የሚገኘውን ጦር አስከትለው ከራስ እምሩ ጋር በትግራይ በኩል በመዝመት ለአገራቸው በጀግንነት ተዋግተዋል። ከማይጨው ውጊያ በኋላ የኢትዮጵያ አርበኞችም ወደኋላ በማፈግፈግና እንደገና በየአካባቢው የሚገኘውን የጎበዝ አለቃ እያስተባበሩ ጠንካራ ውጊያ ለማድረግ ሲዘጋጁ ደጃዝማች መንገሻም የአገው ምድር፣ ሠከላ፣ ሜጫ፣ ጉታ፣ አቸፈር፣ አለፋ ጣቁሳ አካባቢ አርበኞችን በማስተባበር ከወራሪው ጋር መፋለም ጀመሩ።

የጎጃም አርበኞች ራሳቸውን አደራጁ፤ የጦር መሪዎችንም ሾሙ። በዚህ መሰረትም የዘጌ ምድብ ጦር መሪ ፊታውራሪ አምባው ገብረ መድህን፤ የዘጌ መትረየስ ተኳሾች መሪ ፊታውራሪ ከልካይ ሐበሻ፣ የአቸፈር ቆላ ይስማላ ጦር መሪ ፊታውራሪ ደምለው ተፈሪ፤ የአቸፈር ቆላ ይስማላ ጦር መሪ ፊታውራሪ አውደው ሐበሻ፣ ዋና አማካሪና የፕሮፖጋንዳ ስራ ኃላፊ ፊታውራሪ ጊላ ጊዮርጊስ እቁበ ሲሆኑ ከነዚህም በተጨማሪ በሹመቱ ውስጥ ብዙ ታዋቂ ጀግኖችና የጎበዝ አለቆች ነበሩ።

በ1929 ዓ.ም የመጀመሪያ ወር ላይ የጎንደርና የጎጃም አካባቢ የፋሺስት ጦር የበላይ አዛዥ የደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬን መጠናከርና በየአካባቢው የጦር አለቆችን መመደባቸውን ሲሰማ እጅግ ደነገጠ። ይህን የአርበኞችን መጠናከር ሊቋቋምልኝ ይችላል ብሎ ያሰበውን የጦር አዛዥ ሹም ሽር በማድረግና በርካታ ሰራዊት በመመደብ ጦሩ በከተሞች ተወስኖ ምሽግ ይዞ፣ ኃይሉን አጠናክሮ እንዲከላከል አዘዘ።

ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ቢቸናን፣ ራስ ኃይሉ ደብረ ማርቆስንና ሞጣን እንዲሁም ራስ በዛብህ ደግሞ ዳሞት አካባቢን በማካለል የጠላትን ጦር ዓረፍት ነሱት። ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ ከደጃዝማች በላይ ዘለቀና ከሌሎች የውስጥ አርበኞች ጋር በመሆን በከፍተኛ

**ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ በአምስት ዓመቱ የአርበኝነት ተጋድሎ ወቅት ከ40ሺ በላይ አርበኛ በመምራት ባደረጉት ተጋድሎ በበርካታ (ከ30 በላይ) ቦታዎች ከፋሺስት ጦር ጋር ተዋግተው አኩሪ ድሎችን አስመዝግበዋል**

መናበብና መቀናጀት እየተፋለሙ ቀጠሉ።

በአምስት አመቱ የአርበኝነት የትግል እንቅስቃሴ ወቅት የተለያዩ ወታደራዊ ቴክኒኮችን በማስተዋወቅ ረገድ ግንባር ቀደም የሆኑ አርበኞችና በሕዝብ የተመረጡ የጦር መሪዎች ነበሩ። ከነዚህ ተቀባይነት ከነበራቸው የጦር መሪዎች መካከል ራስ አበበ አረጋይ በሸዋ፣ የጎጃሙ በላይ ዘለቀ፣ የአርማጭሆው ውብነህ ተሰማ፣ ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ፣ ነጋሽ በዛብህ፣ ልጅ ኃይሉ በለው ይጠቀሳሉ።

ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ እጅግ ሩህሩህና በውጊያ የተማረኩ ፋሺስቶችንና ባንዳዎችን ጭምር በጥንቃቄና በርህራሄ እንዲያዙና እንዲጠበቁ ከማድረግ ውጭ የከፋ ቅጣት የማይፈፅሙ ሩህሩህ ሰውም ነበሩ። አርበኞች ነፃ ባወጧቸው አካባቢዎች የሚኖረው ሕዝብም ገበሬው እንዲያርስና እንዲያመርት፣ ነጋዴውም እንዲነግድ፣ ቀሳውስቱም ሰዓታትና ቅዳሴውን እንዳያጓድል፣ በሕዝቡ ላይ ምንም ዓይነት በደል እንዳይፈፅም ዳኞችን ሰይመው በበላይነት ይመሩ ነበር።

ደጃዝማች መንገሻ አስደናቂ የጦርና የደህንነት መረጃ አመራር ችሎታም ነበራቸው። የጠላትን እንቅስቃሴ ከውስጥ የሚያወጡና ከውጭ የሚጠቁሙ የመረጃ ሰዎች የሚገናኙባቸው ምስጢራዊ የግንኙነት መዋቅር ዘርግተውም ከመሪ አርበኞች ጋር ይገናኙ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ‹‹ጉታ ገበርማ›› በተባለው ቦታ ከጠላት እጅ የተማረኩ መገናኛዎችንና የመልዕክት ማስተላለፊያ መስመሮችን አገናኝተው አቶ ጊላ ወልደ ጊዮርጊስ (በኋላ ደጃዝማች) በሚባል ብልህ ሰው የሚመራ የስለላና የፕሮፖጋንዳ ኮሚቴ አቋቁመው ነበር፡። በእነዚህ የመገናኛ መሳሪያዎችም የጠላትን እንቅስቃሴ ማዳመጥና የጠላትን የምልክት መገናኛ ኮዶችን መጥለፍ ተችሎ ነበር።

ደጃዝማች መንገሻ በሰላሙ ጊዜ ሩህሩህና ደግ አስተዳዳሪ የመሆናቸውን ያህል በጦርነት ጊዜ ደግሞ ቆራጥ የጦር መሪ እንደነበሩ ታሪካቸው ይመሰክራል። በውጊያ ወቅት የሚያሳዩት ቅልጥፍናና ቆራጥነት የተዋጊ አርበኞቻቸውን ወኔ ከፍ የሚያደርግና በቁጥርም ሆነ በጦር መሳሪያ ብልጫ ያለውን የፋሺስትን ሰራዊት ድል በማድረግ ምርኮ የሚያስቆጥሩ ጀግና የጦር መሪ እንደነበሩ ተደጋግሞ ተመስክሮላቸዋል።

ብልሃትም ሌላው መለያቸው ነበር። በአንድ ወቅት በባሕር ዳር አካባቢ በወራሪው ኃይል ተማርከው የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ከጠላት መንጋጋ መውጣት መቻላቸውን ታሪካቸው ያስረዳል። ከባህር ዳር ከተማ እንዳይለቁ ተብለው የቁም እስረኛ ተደርገው በነበረበት ወቅት የሰከላ፣ የፋግታ፣ የሜጫ፣ የአገው ምድርና የአቸፈር ሕዝብ በምስጢር እየተሰበሰበ የፋሺስት ኢጣሊያን ጦር ለማጥቃት ይነጋገር ነበር። ሕዝቡም ደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬን የጦር መሪ እንዲሆኑ ወሰነ። ጉዳዩ ለደጃዝማች መንገሻ ተነገራቸው። ደጃዝማች መንገሻም በሀሳቡ ተስማምተው በዘዴ አምልጠው ከወጡ በኋላ ሕዝቡን አስተባብረው በፋሺስት ላይ ሸፈቱ።

ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ በአምስት ዓመቱ የአርበኝነት ተጋድሎ ወቅት ከ40ሺ በላይ አርበኛ በመምራት ባደረጉት ተጋድሎ በበርካታ (ከ30 በላይ) ቦታዎች ከፋሺስት ጦር ጋር ተዋግተው አኩሪ ድሎችን አስመዝግበዋል። እነዚህ ከባድ መስዋዕትነት የተከፈለባቸውና አስደናቂ የጀግንነት ጀብዶች የተፈፀመባቸው ውጊያዎች የእነደጃዝማች መንገሻና አርበኞቻቸው የአገር ፍቅር ስሜትና ጀግንነት በተግባር የተገለጠባቸው አኩሪ የታሪክ አሻራዎች ናቸው።

በሰኔ ወር 1932 ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያ አስተዳደር ጣሊያን ከናዚ ጀርመን ጋር ማበሩን ተከትሎ የእንግሊዝ መንግሥት በነበረው የስዊዝ ቦይ ላይ የሚተላለፉ የኢጣሊያ መርከቦች ስንቅ፣ ትጥቅ፣ ሰራዊትና ነዳጅ ጭነው እንዳያልፉ ከለከለ። ይህ የእንግሊዝ እርምጃ የኢትዮጵያን አርበኞች በማበረታትና የፋሺስቶችን አቅም በማዳከም ረገድ ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ አበርክቷል። እናም ኢትዮጵያዊያን አርበኞች በደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ መሪነት ባደረጓቸው አኩሪ ተጋድሎዎች አማካኝነት በርካታ የጎጃም አካባቢዎች ከወራሪው ጦር ነፃ መውጣት ቻሉ።

የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያዊያን አርበኞች ትግል ክፉኛ ተዳክሞ በነበረበት ወቅት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ከሱዳን ተነስተው ወደ አዲስ አበባ ጉዞ እንደ ጀመሩ የጠላት ኃይል በቡሬ ከተማ በተጠናከረ ሁኔታ ምሽግ ሰርቶ ጠበቃቸው። ይህ የጠላት ኃይል መወገድ ነበረበትና ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ ከዳሞቱ መስፍን ደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ ጋር ተቀናጅተው በማጥቃት የጠላት ጦር ቡሬን ለቅቆ እንዲወጣ አደረጉት። በመቀጠልም የፋሺስት ኃይል ሙሉ ጎጃምን ለቅቆ ለመውጣት ተገደደ። ንጉሰ ነገሥቱም በደብረ ማርቆስ በኩል አድርገው ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ።

ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬም በቢትወደድነት ማዕረግ በጎጃም እንደራሴነት በማገልገል ላይ ሳሉ በ1937 ዓ.ም ወደ ሸዋ፣ አዲስ አበባ ተዛውረው በህግ መወሰኛው ምክር ቤት እንደራሴነት እስከ 1938 ዓ.ም ድረስ ካገለገሉ በኋላ የወለጋ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ።

ደጃዝማች ቢትወደድ መንገሻ የወለጋ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ ሆነው በማገልገል ላይ ሳሉ በሰሜኑ ግንባር በሸሬው ጦርነት በቦንብ ፍንጣሪ የቆሰለው አካላቸው ቁስሉ እያመረቀዘ ሲያሰቃያቸው ቆይቶ በእረፍት እጦት ምክንያት በቂ ህክምና ባለማግኘታቸው በ1942 ዓ.ም አረፉ። ስርዓተ ቀብራቸውም በከፍተኛ ክብር በአዲስ አበባ ከተማ በቅድስተ ማርያም ካቴድራል ተፈፅሟል። ደጃዝማች ቢትወደድ መንገሻ ዳንግላ ከተማ ውስጥ በስማቸው ትምህርት ቤት ተሰይሞላቸዋል።

# ስፖርት

## ፕሮጀክቱ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ፌዴሬሽኑ አስታወቀ

ብርሃን ፈይሳ

በስፖርት ውጤታማ ለመሆን መሰረትን በታዳጊዎች ላይ መጣል አስፈላጊ መሆኑ እሙን ነው። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽንም እድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎችን በፓይለት ፕሮጀክት በማቀፍ ሃገርን የሚወክሉ ምርጥ የእግር ኳስ ተጫዋቾችን ለማፍራት በመስራት ላይ ይገኛል። ፕሮጀክቶቹ ከትግራይ ክልል ውጪ ባሉ 27 የሃገሪቷ አካባቢዎች ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ በእዚህም በሁለቱም ጾታ በጥቅሉ 810 የሚሆኑ ታዳጊዎች በስልጠና ላይ ይገኛሉ።

ይህንንም ተከትሎ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ጅራ ፕሮጀክቶቹ ባሉባቸው አካባቢዎች ተገኝተው ጉብኝት በማድረግ የስልጠና ቁሳቁስ እገዛ አድርገዋል። ስልጠናው ከተጀመረ አንስቶ ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለውን ለመመልከት የቻሉት ፕሬዚዳንቱ ተስፋ ሰጪ ሁኔታ የተመለከቱ መሆኑን ፌዴሬሽኑ በድረገጹ አስነብቧል።

ከወዲሁ ትልቅ ተስፋ እያሳዩ ካሉት ታዳጊዎች መካከልም ከ17 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድን አባል ለመሆን የቻሉም አሉበት። ሌሎች ደግሞ በከተማቸው የውስጥ ውድድሮች ላይ ተካፋይ በመሆን ላይ ይገኛሉ። እንደአጠቃላይ ግን ፕሮጀክቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ለመመዘን የሚያስችል ውድድር የቴክኒክ ኮሚቴው በሚያወጣው መርሃ ግብር መሰረት በሃምሌ ወር የሚደረግም ይሆናል።

ከዚህ ቀደም በተለያዩ ስፖርቶች መሰል ፕሮጀክቶች ሲቋቋሙ አስቀድሞ የሚደረግባቸው ዝግጅት አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት ውጤታማ ሳይሆኑ መቅረታቸው ግልጽ ነው። ፌዴሬሽኑም ይህንን ችግር ለመቅረፍ እንዲያስችለው በስፖርቱ እምቅ አቅም ያላቸው አካባቢዎችን የመለየት ኃላፊነቱን ለክልሎች ነበር የሰጠው። ከዚያም የፌዴሬሽኑ ቴክኒክ ኮሚቴ የተሳተፈበት ምርጫ በማድረግ የስልጠና ጣቢያዎቹ ሊቋቋሙ ችለዋል። ስልጠናውም በፊፋ እና በካፍ



**የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ጂራ ለሰልጣኞች ትጥቅ ድጋፍ ሲያደርጉ፣**

ባለሙያዎች በሰለጠኑ አሰልጣኞች እየተሰጠ እንደሚገኝ ፕሬዚዳንቱ ጠቁመዋል።

ከመጫወቻ ኳሶች እና ከስልጠና ቁሳቁስ ጋር በተያያዘም፤ ፌዴሬሽኑ «አንድ ኳስ ለአንድ ሰልጣኝ» በሚል መርህ በአግባቡ የተሟላ ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ጠቁመዋል። በመሆኑም አንድ ሺ ጥራታቸውን የጠበቁ ኳሶች ከሞዛምቢክ እንዲገዙ በማድረግ በተጨባጭ እያንዳንዱ ሰልጣኝ አንድ ኳስ እንዲያገኝ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል።

ሌሎች የስልጠና ቁሳቁስም በተቻለ አቅም ተደራሽ እንዲሆኑ ጥረት እየተደረገ ነው። ይህንንም አስመልክቶ ፕሬዚዳንቱ «ሰልጣኞቹ ወደ ስራ የገቡት በተሟላ ሁኔታ አይደለም። እኛም አስፈላጊው ነገር እንዲሟላላቸው ጥረት እናደርጋለን። ከዚህ አንጻር ከዚህ ቀደም የስልጠና ትጥቅ አሁን ደግሞ የመጫወቻ ኳስ እያሟላን ነው» ማለታቸውንም ድረገጹ አስነብቧል።

ይሁንና በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ አሁንም ድረስ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ችግር ይታያል። በመሆኑም ከክልል ስፖርት ቢሮዎች እንዲሁም ከተማ አስተዳደሮች ጋር መነጋገራቸውንና ይህም እንዲቀረፍላቸው ፕሬዚዳንቱ አመላክተዋል።

አብዛኛዎቹ አካባቢዎች ላይ በቂ ሜዳዎች አሉ፤ ይሁንና የሚያዙት በሌሎች አካላት በመሆኑ ለታዳጊዎቹ ስልጠና ለማመቻቸት አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም የመጠቀሚያ መርሃ ግብር እንዲያዝ ምክክር ተደርጓል። ከማዘውተሪያ ስፍራዎች ባለፈ ሰልጣኞች የላብ መተኪያ ያገኙ ዘንድ ፌዴሬሽኑ ከክልልና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ተወያይቶ ቃል ተገብቶለታል። ወላጆችም የታዳጊዎቹ ትምህርት ላይ ትኩረት ከማድረግ ባለፈ ከስልጠና መልስ ምግባቸው ላይ እንዲያተኩሩም ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

ፌዴሬሽኑ ካቋቋመው ፕሮጀክት ባለፈ በአንዳንድ አካባቢዎች በራሳቸው ተነሳሽነት በትክክለኛው የእድሜ እርከን ተስፋ ሰጪ የሆነ ስልጠና ሲሰጡ የተመለከቷቸው ፕሮጀክቶች መኖራቸውንም ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል። ይህንንም መደገፍ አስፈላጊ በመሆኑ የስልጠና ቁሳቁስ ድጋፍ ከማድረግ ጎን ለጎን የፕሮጀክቱ አካል እንዲሆኑ የተደረገ መሆኑንም አስታውሰዋል።

ይህ ፕሮጀክት በጊዜያዊነት የሚያዝ እንዳልሆነና በዘላቂነት የሚሰራ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ አስታውቀዋል። ይልቁኑ ለአራት ዓመታት በስልጠና ላይ ቆይተው በእድሜ እርከን ለሚቋቋሙ ብሄራዊ ቡድኖች ግብዓት በመሆን በአህጉር እና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ተካፋይ ይሆናሉ። ታዳጊዎች ላይ መስራት የፌዴሬሽኑ ስራ አለመሆኑንም ጠቅሰው፣ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል። የታዳጊዎች እግር ኳስ ልማት የተቀናጀ ስራ እንደሚፈልግ ጠቁመው፣ በአንድ መቆም ያስፈልጋል ሲሉም ፕሬዚዳንቱ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ethio telecom ኢትዮ ቴሌኮም

**INVITATION TO NATIONAL COMPETITIVE BID**
**FLOATING DATE: 20 APRIL 2022**
**RFQ NO, 4083617**

1. Ethio telecom invites all interested and eligible bidders by this National Competitive Bid (NCB) for the procurement of Aluminum Tent Transparent, Aluminum Tent, Conference chair with arm fabric and Round dining table with RFQ No 4083617.

The tender remains floating from April 20,2022 to May 16,2022.

| No. | Item/descriptions | QTY | Unit | RFQ .No | Bid Security Amount |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Aluminum Tent Transparent | 1200 | Square Meter | 4083617 | 200,000.00 |
| 2 | Aluminum Tent | 1200 | Square Meter | | |
| 3 | Conference chair with arm fabric | 200 | pcs | | 50,000.00 |
| 4 | High raised table | 25 | pcs | | |
| 5 | Chair | 50 | pcs | | |
| 6 | Round dining table | 50 | pcs | | |

Bid documents can be obtained from ethio telecom's Head Office, Room No. 201A during office hours (Monday to Friday) upon payment of a non-refundable fee of Birr 100.00 (Birr One hundred only) or you can also find bid documents from web sites www.afrotender.com, www.extratenders.com and www.2merkato.com upon payment of a non-refundable fee of Birr 100.00 (Birr One hundred only) by using tele birr payment platform.

In addition, If you are interested to be on the supplier list of ethio telecom please register using the following link copy and paste the link browser "https://erp.ethiotelecom.et/OA HTML/jsp/pos/suppreg/SupplierRegister.jsp?ouid=0EED8A04B857259C".

2. Interested eligible bidders may obtain further information from ethio's website (i.e. https://www.ethiotelecom.et/tender/).

2.1. Sealed bids marked as: "Tender for the Supply of Aluminum Tent Transparent, Aluminum Tent, Conference chair with arm fabric and Round dining table with RFQ No. 4083617 and be addressed to:

**Ethio telecom,**
**Head Quarter**
**Supply Chain Division**
**2nd Floor, Room No.211B,**
**P. O. Box 1047, Addis Ababa, Ethiopia**

2.2. Bid proposal will be received at ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No. 211B, Before or on May 16,2022, 5:00 P.M. Bids presented by any bidder after the closing date shall not be accepted.

3. Bids received in time and fulfilling the other formalities shall be opened in the presence of interested bidders or their legal representatives on May 17, 2022, at 10:00 A.M, at ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No.201A.

4. Ethio telecom reserves the right to reject all or parts of this bid.

5. Partial bid is allowed.

**Ethio Telecom**